አጋሮች/ Partners

በስ.ጉ.ኤ የተተገበረ
Implemented by ARRA

በአውሮፓ ህብረት ገንዘብ ተደገፈ
Financed by the European Union


## ምስጋና

ይህ ማኑዋል የተዘጋጀው በከስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲ የስደት ተመላሾች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት አማካኝነት በአውሮፓ ህብረት የገንዘብ ድጋፍ ነው። የፌዴራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ በማኑዋል ዝግጅቱ ላይ ለተሳተፉ ባለሙያዎች፣ አስተዋጾ አድራጊዎች፣ አራሚዎችና አጋሮች ጥልቅ ምስጋናውን ይገልፃል።


## ማሳሰቢያ

ይህ ማኑዋል የተዘጋጀው በአውሮፓ ህብረት የገንዘብ ድጋፍ ነው። በመሆኑም በሰነዱ ላይ የተካተቱ ሀሳቦች በሙሉ የፌደራል የከተሞች የስራ ዕድል ፈጠራና የምግብ ዋስትና ኤጀንሲ ብቸኛ ኃላፊ ሲሆን በየትኛዉም መልኩ የአውሮፓ ህብረትን እና የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች ጉዳይ ኤጀንሲን ሃሳብ ወይም አቋም የሚያንፀባርቅ አይደለም።

# ማውጫ


መግቢያ ---------- 1

ክፍል አንድ፦ የሂሳብ አያያዝ አጠቃላይ ሁኔታ ---------- 2

1.1 የሂሳብ መዝገብ አያያዝ እና የሂሳብ አያያዝ ትርጉም ---------- 2

1.1.1 የሂሳብ መዝገብ አያያዝ /Book-Keeping/ ---------- 2

1.1.2 የሂሳብ አያያዝ /Accounting/ ---------- 2

1.2 ዓላማ ---------- 3

1.3 ጥቅም ---------- 3

1.4 የሂሳብ አያያዝ ዋና ዋና የቁጥጥር መርሆዎች ---------- 4

ክፍል ሁለት፦ የኢንተርፕራይዝ የሂሳብ ሹም እና የሂሳብ አያያዝ ---------- 5

2.1 የሂሳብ አያያዝ ድጋፍ ሰጪና ክትትል ባለሙያ ተግባር እና ኃላፊነት ---------- 5

2.1.1 ኃላፊነት ---------- 5

2.1.2 ተግባር ---------- 5

2.2 የኢንተርፕራይዞች የሂሳብ ሹም ተግባር እና ሀላፊነት 6

2.2.1. ኃላፊነት ---------- 6

2.2.2. ተግባር ---------- 6

ክፍል ሦስት፦ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አደረጃጀት እና የዘርፍ ዓይነቶች 7

3.1 የአደረጃጀት ዓይነቶች ---------- 7

3.1.1 የንግድ ድርጅት ---------- 7

3.2 የንግድ ስራ ዘርፍ ዓይነቶች ---------- 8

3.2.1 የምርት ስራ /manufacturing/ ---------- 8

3.2.2 አገልግሎት /service/ ---------- 8

3.2.3 ንግድ /trade/ ---------- 9

ክፍል አራት፦ የሂሳብ አያያዝ ---------- 10

4.1 የሂሳብ አያያዝ ዘዴዎች ---------- 10

4.2 መሰረታዊ የሂሳብ አያያዝ ስርዓቶች እና አገልግሎታቸው ------------------------ 11
4.2.1 የሂሳብ አያያዝ መሰረቶች ------------------------------------------------ 11
4.3 የሂሳብ አርዕስቶች እና መለያ ቁጥሮች --------------------------------------- 14
4.3.1 የሂሳብ አርዕስቶች --------------------------------------------------------- 14
4.3.2 የሂሳብ መለያ ቁጥር --------------------------------------------------------- 16
4.4 መሰረታዊ የሂሳብ አያያዝ ቀመር እና የሂሳብ መነሻ ሚዛን -------------------- 17
4.4.1 መሰረታዊ የሂሳብ አያያዝ ቀመር ------------------------------------------- 17
4.4.2 የሒሳብ መነሻ ሚዛን /opening balance/ ------------------------------ 18
4.5 የሂሳብ አያያዝ ሑደት ------------------------------------------------------- 18
ክፍል አምስት፦ ታክስ /ግብር/ ------------------------------------------------------ 29
5.1 የታክስ ምንነት እና አስፈላጊነት ---------------------------------------------- 29
5.2 የታክስ አወቃቀር ------------------------------------------------------------- 29
5.3 የታክስ ሂሳብ አያያዝ (tax accounting) -------------------------------------- 31
5.3.1 የንግድ ሥራ ገቢ ታክስ/ግብር ---------------------------------------------- 31
5.3.2 የቅድመ ንግድ ትርፍ ግብር ክፍያ (withholding tax) ---------------- 32
5.3.3 ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች ------------------------------------------------ 33
5.3.4 ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች -------------------------------------------- 33
5.3.5 ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክስ (VAT and ToT) ------- 34
5.3.5.1 ተጨማሪ እሴት ታክስ ምጣኔዎች ---------------------------- 35
5.3.5.2 ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የተደረጉ ግብይቶች ------------- 36
5.3.5.3 ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ------------------------------- 37
5.3.5.4 የተጨማሪ እሴት ታክስን መመዝገብ ------------------------- 37
5.3.5.5 ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ላይ ተቀናሽ ተደረጎ ስለ ሚያዝ ታክስ 39
5.3.5.6 ተርን ኦቨር ታክስ ------------------------------------------------ 39
5.3.5.7 ከተርን ኦቨር ታክስ ነፃ የተደረጉ ግብይቶች ------------------ 40
5.3.5.8 ሌሎች ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች ------------------------------- 40
ምሳሌዎች ------------------------------------------------------------------------- 42

# መግቢያ

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ከግብርናው ቀጥሎ ሠፊ የስራ ዕድል በመፍጠር የዜጎችን ገቢና የኑሮ ደረጃ በማሻሻል ድህነትንና የስራ አጥነትን በመቀነስ ረገድ ከፍተኛ ሚና እያበረከተ ይገኛል፡፡ ዘርፉ ከስራ ዕድል ፈጠራው ጎን ለጎን ዜጎች ዘመናዊ የንግድ ስርዓት ውስጥ ገብተው ብቁና ተወዳዳሪ በመሆን ለኢንዱስትሪው ልማት መሰረት እንዲጥሉ ለማስቻል የንግድ ዕቅድ ዝግጅት፣ ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ስርአት ዝርጋታና የሂሳብ ምርመራ፣ የቴክኒክ ክህሎት ስልጠና፣ የፋይናንስ፣ የማምረቻና መሸጫ ቦታ፣ የኢንዱስትሪ ኤክስቴንሽን እና የገበያ ትስስር ድጋፎችን በማቅረብ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በዚህ መሰረት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚሰጣቸውን መንግስታዊ ድጋፎች በተገቢ ሁኔታ ተጠቅመው በምርትና አገልግሎት እንቅስቃሴያቸው ከጊዜ ወደ ጊዜ ዕድገት በማሳየታቸው ካሉበት ደረጃ ወደሚቀጥለው የእድገት ደረጃ እንዲሸጋገሩ እየተደረገ ይገኛል፡፡ ይሁንና የኢንተርፕራይዞች የእድገት ደረጃ ሽግግር ለማከናወንም ሆነ ያሉበትን የንግድ እንቅስቃሴ የሚያሳይና ሀብትና ንብረታቸውን ለማወቅ የሚያስችል ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ተግባራዊ እንዲያደርጉ የሚያስችሉ ድጋፎች ባለፉት ዓመታት ሲሰጥ የቆየ ቢሆንም የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ከማዘጋጀትና ከማውጣት አንጻር ብዙ ችግሮች እያጋጠሙ ይገኛሉ፡፡ ሆኖ ቆይቷል፡፡ በመሆኑም ኢንተርፕራይዞቹ በኢኮኖሚው ዕድገት ውስጥ የሚኖራቸው አስተዋፅኦ ከፍተኛና አስተማማኝ እንዲሆን ስርዓቱን የበለጠ አጠናክሮ ለመቀጠልና በዘርፉ የተመደቡ ባለሙያዎች አቅም ለማጠናከር የሚያስችል የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ አያያዝ ማሳያ ማንዋል ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡

በዚሁ መሰረት አዲስ የሚቋቋሙ እና የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የገንዘብና የንብረት አስተዳደራቸው አስተማማኝ እንዲሆን፣ በመንግሥት በኩል የሚፈለግባቸውን ግዴታዎች መወጣታቸውን ለማረጋገጥ፣ ሌሎች አካላት በእንቅስቃሴያቸው ላይ እምነት ማሳደር እንዲችሉ፣ የሚደረግላቸው ድጋፍም አቅማቸውን ያገናዘበ እንዲሆን ለማስቻል ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት እንዲከተሉ ለማድረግ እና በዘርፉ የተመደቡ ባለሙያዎችን ተግባርና ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እንዲወጡ ለማገዝና ስራውን የበለጠ ለማሳለጥ እንዲቻል ይህ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ አያያዝ ማሳያ ማንዋል ተዘጋጅቷል፡፡

# ክፍል አንድ፦ የሂሳብ አያያዝ አጠቃላይ ሁኔታ

## 1.1 የሂሳብ መዝገብ አያያዝ እና የሂሳብ አያያዝ ትርጉም

### 1.1.1 የሂሳብ መዝገብ አያያዝ /Book-Keeping/

የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ማለት ማንኛውም የንግድ ድርጅት የሂሳብ ልውውጦችን በሂሳብ አያያዝና አሰራር ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት አግባብ ባላቸው ሰነዶች መዛግብት ስርዓት ባለው ሁኔታ የሚመዘገብበትና የሂሳብ መረጃዎችንም የሚይዝበት የአሰራር ጥበብ ነው፡፡ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ማለት በአጭሩ የሂሳብ ክስተቶችን በሂሳብ ሰነዶችና መዝገቦች ላይ መመዝገብ ማለት ነው፡፡

### 1.1.2 የሂሳብ አያያዝ /Accounting/

የሂሳብ አያያዝ ማለት በማንኛውም የንግድ ተቋም ውስጥ የሚገኙትን የኢኮኖሚ መረጃዎች ለመመዝገብ ለማብራራትና ለተጠቃሚው ክፍል ለማስተላለፍ የሚያገለግል የንግድ ዓለም ቋንቋ ነው፡፡ ስለሆነም የሂሳብ አያያዝ የሚያከናውናቸው ተግባራቶች ሰፊ በመሆናቸው አንድ ወጥ ትርጉም ለመስጠት ቢያዳግትም የሂሳብ አያያዝን ጠቅለል ባለ መልኩ እንደሚከተለው መተርጎም ይቻላል፡፡

በሂሳብ መዝገብ አያያዝ የተከናወኑና የሚከናወኑ ተግባራት ወቅታዊና አስተማማኝነት የማረጋገጥና የመቆጣጠር እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ተከትሎ የሂሳብ መረጃዎችን በማቀነባበር የስራ እንቅስቃሴ ውጤት በትክክል የሚገልፁ የሂሳብ መግለጫዎችንና ሪፖርቶችን የማዘጋጀት፣ የመተንተን፣ የመተርጎምና ለሚመለከታቸው ክፍሎችም እንዲደርሱ የማድረግ ተግባራት የሚከናወንበት የሂሳብ አሰራር ስርዓት ወይም የሂሳብ አያያዝ /Accounting/ ይባላል፡፡

ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ መዝገብ አያያዝ/Book-Keeping/ እና የሂሳብ አያያዝ (Accounting) ሳይነጣጠሉ በሂሳብ ባለሙያው የገበያ ልውውጦችን /ክስተቶችን / የመመዝገብ፣ የመለየት፣ የማቀናጀት፣ የመተርጎም፣ የመተንተና መረጃውን ለሚያስፈልጋቸው አካላት ሪፖርት የማድረግ ሂደት ይከናወናል፡፡

የሂሳብ አያያዝ (Accounting) የገበያ ልውውጥ /ክስተቶች /የመመዝገብ፣ የመለየት፣ የማቀ ናጀት፣ የመተርጎም፣ የመተንተንና መረጃውን ለሚያስፈልጋቸው አካላት ሪፖርት የማድረግ ሂደት ነው፡፡

## 1.2 ዓላማ

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከግምታዊ አሰራር ተላቀው፣ ዘመናዊ የንግድ ስርዓት እንዲከተሉ እና የውስጥ ቁጥጥር ስርዓታቸው እንዲጠናከር በማድረግ በየስራ ዘመኑ በተደረገው የስራ እንቅስቃሴ የተገኘውን ውጤት በመለካት በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔዎችን መስጠት እንዲችሉ ማድረግ ነው።

## 1.3 ጥቅም

የሂሳብ አያያዝ የአንድን ተቋም/ ድርጅት ጥንካሬና ድክመት የሚመዝን ዋና መሳርያ ሲሆን ወደፊት ለምናወጣው ዕቅድ ሆነ የስራ አመራር ውሳኔ መነሻ ሲሆን የሚከተሉት ዝርዝር ጥቅሞች ይኖሩታል።

- በኢንተርፕራይዞች የአሰራር ህጎች፣ ደንቦችና መመሪያዎች መሰረት እንዲከናወኑና አመራሩ ከግላዊ አመለካከቶች ተፅዕኖ ነፃ በመሆን ቀጥተኛና ግልፅ የሆነ ውሳኔ እንዲሰጥ ያደርጋል፣
- ገቢና ወጪ ሂሳቦችን በትክክል በመመዝገብ የድርጅቱን የፋይናንስ እንቅስቃሴ ሂደት ለማወቅ ይረዳል።
- ግልፅ፤ ቀላልና ስርዓትን የተከተለ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መኖሩ ጊዜን እንዲቆጠብ ያደርጋል፣
- ድርጅቱ በሚያደርገው የንግድ እንቅስቃሴ ትርፍ ወይም ኪሳራ እንደደረሰበት ለማወቅ ይረዳል፣
- የገንዘብና ንብረት ምዝበራና ስርቆትን ለማስወገድ ይረዳል፣
- አላስፈላጊ ወጪዎችን ለመቆጣጠር ያግዛል፤
- ወቅታዊ የሃብት ግምት ሁኔታ እንድናውቅ ያደርጋል፣
- የሚሰበሰቡና የሚከፈሉ ዕዳዎችን በጥንቃቄ እንዲያዙ ይረዳል፣
- ትርፍን ሊያስገኝ የሚችል የመሸጫ ዋጋ ለመተመን ይረዳል፣
- ተቋሙ ለገባቸው ግዴታዎች ለመገዛት እና በቀረጥ ህጎች መሰረት ኃላፊነቱን ለመወጣት ያስችላል፣
- ከሌሎች አቻ ተቋማት ጋር ቀልጣፋና አስተማማኝ የሆነ የስራ ግንኙነት እንዲዘረጋ ያደርጋል፣
- ለንግድ ስራው የሚያስፈልገውን ጥሬ ገንዘብ በበቂ ሁኔታ መኖሩንና አለመኖሩን፣ ተሰብሳቢና ተከፋይ እዳዎችን ወዘተ... በቀላሉ ለመለየት ስለሚረዳ ኢንተርፕራይዞች መውሰድ የሚገባቸውን እርምጃ ይጠቁማል፣
- ግዴታን ለመወጣት ይረዳል።

## 1.4 የሂሳብ አያያዝ ዋና ዋና የቁጥጥር መርሆዎች

- ማንኛውም የገንዘብ እንቅስቃሴ መከናወን የሚገባው በገንዘብ መቀበያና በወጪ ማዘዣና የክፍያ ደረሰኞች ብቻ መሆን አለበት።
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለከፈሉት ክፍያ ማስረጃ መቀበልና ለሰበሰቡት ገቢም በወቅቱ ህጋዊ ደረሰኝ መስጠት ይኖርባቸዋል።
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ገቢና ወጪያቸውን በተገቢው መዛግብት ላይ በወቅቱ መመዝገብ ይኖርበታል።
- የኢንተርፕራይዙ ንብረቶች ተገዝተው ወደ ንብረት ክፍል ሲገቡም ሆነ ሲወጡ በእቃ ገቢ እና ወጪ ደረሰኝ መስፈር ይኖርባቸዋል።
- በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ገንዘብ ወጪ እንዲሆን የሚፈቅድ አመራር ወይም ኃላፊ ገንዘብ አይሰብስብም፣ የሂሳብ መዝገብ ስራም አያከናውንም።
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በዓመቱ መጨረሻ የትርፍና ኪሳራ እና የሀብትና ዕዳ መግለጫ ማዘጋጀት ይኖርበታል።
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ሂሳባቸውን ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ ማስመርመር እና የምርመራውንም ውጤት በአንድ ወር ጊዜ ውስጥ ለጠቅላላ አባላቱ ማቅረብ አለበት።
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ሂደትን በተመለከተ ገንዘብ በአግባቡ ለመጠቀምና ከብክነት ለመጠበቅ እንደ ኢንተርፕራይዙ የእድገት ደረጃ በኢንተርፕራይዞቹ የሚወሰን ከብር 5,000. ያልበለጠ የገንዘብ መጠን በካዝና /በእጅ ማሳደር የለባቸውም ፣
- የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለጥቃቅን ወጪዎች ብቻ የሚሆን ብር 1,000. በገንዘብ ያዥ እጅ ሲኖር ሌሎች ክፍያዎች በቼክ መከፈል አለባቸው፣
- ገንዘብ ያዡ በተገቢው ባለስልጣን ወጪ መፈቀዱን ሳያረጋግጥ ክፍያ መፈፀም የለበትም።
- ለወጪ መፍቀድ ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም የማህበሩ አመራር የገንዘብ መሰብሰብ ስራ ላይ ሊሰማራ አይችልም፤ በተጨማሪም የሂሳብ ምዝገባ ስራም አያከናውንም።

# ክፍል ሁለት፦ የኢንተርፕራይዝ የሂሳብ ሹም እና የሂሳብ አያያዝ የድጋፍ ሰጪ ባለሙያዎች ተግባርና ኃላፊነት

ኢንተርፕራይዞች ተደራጅተው ወደ ስራ እንደገቡ የስራውን ቀጣይነት ለማረጋገጥ ወይም ስራው በአግባቡ ለመስራት እንዲቻል ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ዘዴዎችን በተሟላ ሁኔታ መዘርጋት ይጠበቅባቸዋል:: ይህንን ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ዘዴ በተሳካ ሁኔታ እንዲያከናውኑ በየደረጃው ያሉ ባለድርሻ አካላት የየራሳቸውን ድርሻ መወጣት የሚገባቸው ቢሆንም በቀጥታ ስራው የሚመለከታቸው የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ልማት ዘርፍ ውስጥ ያሉ የሂሳብ አያያዝ ድጋፍ እና ክትትል ባለሙያዎች እና የኢንተርፕራይዝ የሂሳብ ሹሞች ተግባር እና ኃላፊነት እንደሚከተለው ተዘርዝሯል::

## 2.1 የሂሳብ አያያዝ ድጋፍ ሰጪና ክትትል ባለሙያ ተግባር እና ኃላፊነት

### 2.1.1 ኃላፊነት

- ለኢንተርፕራይዝ አባላት/ለስራ አስፈፃሚ ኮሚቴ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ጥቅም ግንዛቤ ማስጨበጥ፣
- የኢንተርፕራይዞቹን የሂሳብ ሹም የሂሳብ አያያዝ ዘዴዎችን እና አተገባበር ግንዛቤ ማስጨበጥ::
- ለሂሳብ አያያዝ ስርዓት ዝርጋታ የሚያስፈልጉ መዛግብት፤ የሂሳብ ሰነዶችን እና ሌሎች መረጃዎች እንዲሟሉ ያስደርጋል::
- ስለገቢና የወጪ ደረሰኝ አጠቃቀም፣ ህጋዊነትና አተገባበር ላይ ለሚመለከተው አካላት ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፣
- ከክፍያ ላይ ስለሚቀነስ የተጨማሪ እሴት ታክስ እና የትርፍ ግብር የቅድመ ክፍያ ካለ ትክክለኛ ደረሰኝ መቀበሉን እና ይህንኑ በወቀቱ ከሚከፈለው ግብር ላይ ተቀናሽ የሚደረግ መሆኑን ግንዛቤ እንዲያገኙ ያደርጋል::
- የድጋፍ ሰጪ ባለሙያው የሂሳብ አያያዝ ሙያዊ ስነምግባርን /proffessional Ethics/ በጠበቀ ሁኔታ ስራዎችን ማከናወን፣
- የድጋፍ ሰጪ ባለሙያው ከቴክኒክና ሙያ ጋር በመሆን ኢንተርፕራይዞችን በጋራ ይደግፋሉ፣
- ባለሙያው እራሱን ወቅታዊ ለማድረግ ከተቋሙ እና ከተቋሙ ውጪ ከሂሳብ አያያዝ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን መመሪያዎች፣ አዋጆች እና ሌሎች መረጃዎችን እና ቴክኖሎጂዎች በመከተል ማብቃት ይኖርበታል::

### 2.1.2 ተግባር

- በሂሳብ አያያዝ የሚከናወኑ ስራዎችን እቅድ ያዘጋጃል፣ ሪፖርት ያቀርባል::
- ለሂሳብ አያያዝ ተግባራት ስራ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች እንዲሟሉለት ያደርጋል::
- የሂሳብ አያያዝ ስርዓት አተገባበር በተግባር መዝግቦ በማሳየት ኢንተርፕራይዞች ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይከታተላል::

- የስራ አስፈጻሚዎች በተሰጣቸው የስራ ድርሻ መሰረት ስራቸውን እንዲያከናውኑ ድጋፍ ያደርጋል፣
- በየሶስት ወሩ የኢንተርፕራይዙን የባንክ አካውንት እና የሂሳብ መዝገብ እንዲታረቅ ድጋፍ ያደርጋል።
- የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ተዘርግቶላቸው ተግባራዊ ያደረጉ ኢንተርፕራይዞችን መረጃ ያደራጃል፣ ይተነትናል የኢንተርፕራይዙ የሂሳብ አያያዝ ሁኔታ ያለበትን ደረጃ ለይቶ ያስቀምጣል፣ እንደ አስፈላጊነቱ የመፍትሄ ወይም የእርምት ሃሳቦችን ያቀርባል።

## 2.2 የኢንተርፕራይዞች የሂሳብ ሹም ተግባር እና ሀላፊነት

### 2.2.1. ኃላፊነት

- የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ዝርጋታ እና አተገባበር ከሚመለከተው አካል ግንዛቤ መውሰድ አለባቸው።
- ለሂሳብ አያያዝ ስርዓት ዝርጋታ የሚያስፈልጉ መዛግብት፤ የሂሳብ ሰነዶች እና ሌሎች ለሂሳብ አያያዝ ስራ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ማሟላት ይጠበቅባቸዋል።
- ለከፈሉት ገንዘብ ተገቢውን ደረሰኝ በመቀበል እንዲሁም ለፈጸሙት ሽያጭ ተገቢውን ደረሰኝ በመስጠት ደረሰኙን መነሻ በማድረግ የሂሳብ ምዝገባ እንዲከናወን የማድረግ።
- ከጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት ከተላከ ድጋፍ ሰጪ ባለሙያ ጋር ተባብሮ መስራት።
- የተዘጋጀ የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት እንዲሁም የኦዲት ሪፖርት ለጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዝ ልማት ጽ/ቤት ማቅረብ።

### 2.2.2. ተግባር

- የስራ ዕቅድና በጀት በማዘጋጀት በሚመለከተው ኃላፊ ያፀድቃል፡
- የወጪና የገቢ ደረሰኞችን በማዘጋጀት በዋና የሂሳብ መዝገብ እና የሂሳብ ቋቶች ያስተላልፋል፣
- የስራ እና የሂሳብ ሪፖርቶችን በማዘጋጀት በኢንተርፕራይዙ ስራ አስኪያጅ/ሊቀመንበር ያፀድቃል፣ ለሚመለከታቸው አካላት ያቀርባል፣
- ወርሃዊ የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ ያዘጋጃል፣
- ለማንኛውም ግዢዎች ህጋዊ ደረሰኝ መቅረባቸውንና የንብረት ገቢ ደረሰኝ መዘጋጀቱን በማረጋገጥ የወጪ ደረሰኝ ያዘጋጃል፣
- ወቅታዊ የንብረትና የገንዘብ ቆጠራ በማድረግ ከሂሳብ መዝገቦች ጋር ያመዛዝናል፣የገንዘብ እና የንብረት ያዥ የስራ አፈፃፀማቸውን ሞልቶ ያፀድቃል
- ደሞዝና ሌሎች ክፍያዎች ሲፈፀሙ በኢንተርፕራይዙ መተዳደሪያ ደንብ እና በጠቅላላ ጉባኤ መወሰናቸውን በማረጋገጥ እና ሂሳቡን በትክክል በማስላት ለሚመለከተው ክፍያ እንዲፈፀም ያደርጋል።

# ክፍል ሦስት፦ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች አደረጃጀት እና የዘርፍ ዓይነቶች

## 3.1 የአደረጃጀት ዓይነቶች

### 3.1.1 የንግድ ድርጅት፡-

የንግድ ድርጅት ማለት በጥቃቅንና አነስተኛ ለትርፍ የተቋቋመ ኢንተርፕራይዝ ሲሆን ከንግድ ሕግ/ስርዓት ጋር የተያያዙ ውሎች፣ልውውጦች እና የንብረት ባለቤትነት መብቶች የያዘ ነው፡፡

የንግድ ድርጅቶች ሕጋዊ ሰውነት የተሰጣቸው በመሆናቸው ከአበዳሪዎቻቸውና ከደንበኞቹ ብቻ ሳይሆን ከንግዱ ባለቤቶቹ ጭምር ለሂሳብ አያያዝ እንዲያመች መለየት ይኖርባቸዋል፡፡

ስለሆነም ንግዱ የሚጠቀምባቸውን የሂሳብ ሰነዶች እና የሂሳብ መግለጫዎች በሙሉ ማመላከት ያለባቸው የንግድ ስራውን ብቻ ነው፡፡ የንግድ ስራዎች አደረጃጀት በባለቤትነት በግል፣ በህብረት ሽርክናና ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማህበራት አማካኝነት ሊቋቋሙ የሚችሉ ሲሆን በንግድ ስራ እንቅስቃሴያቸው በኢንዱስትሪ (ማኑፋክቸሪንግ፣ ኮንስትራክሽንና ማዕድን)፣ በአገልግሎት (ንግድ) እና በግብርና (የከተማ ግብርና) በሚል ይመደባሉ፡፡

በጥቃቅንና አነስተኛ የሚደራጁ ኢንተርፕራይዞችን አደረጃጀት በሁለት መልኩ ከፍለን መመልከት እንችላለን፡፡ እነርሱም፡-

ሀ. በግል የሚቋቋም ኢንተርፕራይዝ እና

ለ. በንግድ ሕግ መሰረት የሚቋቋም የንግድ ማህበር ናቸው፡፡

#### ሀ. በግል የሚቋቋም ኢንተርፕራይዝ

የግል ኢንተርፕራይዝ አንዱ የአደረጃጀት አይነት ሲሆን የኢንተርፕራይዙ አጠቃላይ እንቅስቃሴ እና ስራዎች በሙሉ ኢንተርፕራይዙ ባቋቋመው አቅምና ፍላጎት የሚወሰን ይሆናል፡፡

#### ለ. በንግድ ማህበር የሚቋቋም ኢንተርፕራይዝ

በሀገራችን ተጨባጭ ሁኔታ ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የሚመሰረቱባቸው በኅብረት ሽርክና ማኅበር፣ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር ሲሆኑ የኢንተርፕራይዞች አደረጃጀትም በአብዛኛው በእነዚህ ላይ የተመሰረተ ይሆናል፡፡

### የኅብረት ሽርክና ማኅበር

የኅብረት ሽርክና ማህበር አደረጃጀት ሕጋዊ ሕልውና ያለው በንግድ ሕጉ ካሉት የንግድ ማኅበራት ዓይነቶች ሁሉ ቀላል ቅርጽ ያለው አደረጃጀት ነው። በህብረት ሽርክና አደረጃጀት የሸሪኮች አነስተኛ ቁጥር ሁለት ብቻ ሲሆን የአነስተኛ ካፒታል ጥያቄ ገደብ የለበትም። ካፒታሉ በውስጠ ደንቡ ውስጥ ቢካተትም ከምዝገባ በፊት መክፈሉ አስፈላጊ አይደለም። የሙያ ወይም የአገልግሎት መዋጮ የተፈቀደ ነው።

### ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር

ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ማኅበር በንግድ ከሁለት አባላት ባላነሰ ከሃምሳ አባላት ባልበለጠ የሚቋቋም ሆኖ የማህበሩ መነሻ ካፒታል ከብር አስራ አምስት ሺ ያላነሰ፣ የማህበሩ አክሲዮን እኩል በሆነ የአክሲዮን ዋጋ የተከፋፈለ ሆኖ የአንድ አክሲዮን ዋጋ ከብር አስር ያላነሰ ሲሆን አባላቱም የተወሰነ ኃላፊነት ያለባቸው ድርጅት/ማህበር ነው።

## 3.2 የንግድ ስራ ዘርፍ ዓይነቶች

በጥቃቅንና አነስተኛ የሚደራጁ ኢንተርፕራይዞች የሚሰማሩባቸው የስራ ዘርፍ ዓይነቶች ሶስት ሲሆኑ እነርሱም ኢንዱስትሪ ፣ ግብርና እና አገልግሎት ዘርፎች ናቸው። እነዚህን የስራ ዘርፍ ዓይነቶች ያላቸውን የግብይት ሰንሰለት ቀጣይነት እንዲኖረውና እንቅስቃሴያቸው እንዲያድግ ዘመናዊ የሆነ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ሊኖራቸው ይገባል። በዚህም መሰረት ለማሳያነት የተለመዱ የሂሳብ አያያዝ የንግድ ስራ ዓይነቶች (የምርት ስራ፣የንግድ እና አገልግሎት) እንደሚከተለው ቀርቧል።

### 3.2.1 የምርት ስራ /manufacturing/

ምርት ማምረት፡- የሰው ሃይልና ሌሎች ግብዓቶችን በመጠቀም ጥሬ ዕቃን ወደ ምርት በመቀየር ለሽያጭ ማቅረብ ማለት ነው።

በምርት ስራ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የሂሳብ አያያዝ ከሌሎች ከማምረት ስራ ውጪ ያሉ ኢንተርፕራይዞች የሚለያቸው በስራ ሂደት/process/በጥሬ ዕቃ /raw material inventory/ እንቅስቃሴያቸው ነው። እነርሱም፡-

- ✓ ስራ ላይ ያልዋለ /raw material inventory/
- ✓ በምርት ሂደት ላይ ያለና /work in process/
- ✓ የተጠናቀቀ ምርት /finished goods/ በመባል ይታወቃሉ።

### 3.2.2 አገልግሎት /service/

የአገልግሎት ዘርፍ የሚባለው በኢኮኖሚ ንዑስ ክፍል ውስጥ የሚታወቅ የንግድ ዓይነት ሲሆን ባህሪውም ከሌሎች የንግድ ስራ ባህሪዎች ጋር ቢመሳሰልም አቅርቦቱ በልዩ ሁኔታ ሙያዊ

ተግባራት ለደንበኞች የሚሰጥበት ነው፡፡ አንድ ኢንተርፕራይዝ በመግዛትም ሆነ በመሸጥ ረገድ ለምርቶች እና ለአገልግሎቶች የሂሳብ አያያዝ በርካታ ተመሳሳይነት ይዘት ያላቸውን የሂሳብ አርዕስቶች ሊገነዘብ ይችላል ፡፡ በሁለቱም ሁኔታዎች አንድን ምርት ወይም አገልግሎት በመሸጥ የሚያገኘው ገንዘብ በስራ ላይ እንደተገኘ ገቢ /operating income/ ሆኖ ይቆጠራል፡፡ በተመሳሳይም በምርቶች እና አገልግሎቶች ላይ ያወጣው ገንዘብ እንደ ወጪ ሆኖ ወደ አንድ የተወሰነ የወጪ መደብ ውስጥ ይወድቃል፡፡

አገልግሎት ዘርፍ ከሌሎቹ የሚለይበት ዋነኛው ምክንያት የሚጨበጥ ኢንቬንቶሪ /stock/ አለመኖሩ ነው፡፡ ይህም ማለት የምርት ስራ ዘርፍ እና የንግድ ዘርፍ የተመረቱ ወይም ሊጨበጡ የሚችሉ ምርቶችን ሲሸጡ በአገልግሎት በኩል ግን ይህንን ማድረግ አይቻልም፡፡ ለአብነትም የአገልግሎት ዘርፍ ከሚሰጣቸው አገልግሎቶች ውስጥ ሕክምና፣የሕግ አገልግሎት፣ ማማከር ስራ ተጠቃሾች ናቸው፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የአገልግሎት ዘርፍ ከሌሎች የስራ ዘርፎች አንፃር ሲታይ የሂሳብ መግለጫው ቀለል ባለ ሁኔታ የቀረበ መሆኑ ነው፡፡ በቀላሉ ለማሳየት ያህል የትርፍ እና ኪሳራ መግለጫው ላይ በመጀመሪያ ሽያጭ ሲመዘገብ በመቀጠል በበጀት ዓመት ውስጥ የወጡ ወጪዎችን በመመዝገብ እና ሁለቱን በማቀናነስ ትርፍ/ኪሳራ ማግኘት ይቻላል፡፡

## 3.2.3 ንግድ /trade/

ንግድ ማለት አንድ ኢንተርፕራይዝ/ድርጅት በተሰማራበት የንግድ ዘርፍ ከሌላ የንግድ ዘርፍ/አምራች በጅምላ ወይም በችርቻሮ ሸቀጦችን የመግዛት፣ የመሸጥ ወይም የመለዋወጥ ድርጊት ወይም ሂደት ሲከናወን ንግድ ብለን እንጠራዋለን፡፡ የንግድ ዘርፍ እንደ ሌሎቹ የጥቃቅንና አነስተኛ የተደራጁባቸው ዘርፎች ሁሉ የሂሳብ አያያዝን በመጠቀም እንቅስቃሴውን ማጎልበት ይቻላል፡፡ ይህ ዘርፍ ከአገልግሎት ዘርፍ የሚለየው የቁሳቁስ ክምችት /stock/ በመኖሩ ምክንያት ነው፡፡ የንግድ ኢንተርፕራይዞች ዋነኛው ሥራቸው ዕቃዎችን ከአቅራቢዎች በመግዛት ሸቀጦቹን ቅርፅ ሳይቀይሩ ለሸማቾች የሚሸጡ ናቸው፡፡ ለአብነትም የሸቀጣሸቀጥ ሱቆች እና ሱፐር ማርኬቶች ይጠቀሳሉ፡፡ እነዚህ በንግድ ዘርፍ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች የዕለት ተዕለት ፍላጎቶችን ከአቅራቢዎች ይገዙና ለሸማቾች እንደገና ይሸጣሉ፡፡

# ክፍል አራት፦ የሂሳብ አያያዝ

## 4.1 የሂሳብ አያያዝ ዘዴዎች

የሂሳብ አያያዝ /አመዘጋገብ ዘዴ በሁለት ይከፈላሉ፣

1. ነጠላ የሂሳብ አመዘጋገብ እና
2. መንትያ የሂሳብ ዘዴ ናቸው::

### 1. ነጠላ የሂሳብ አመዘጋገብ ዘዴ:-

ክፍያን ወይም ገቢን አንድ ጊዜ ብቻ የሂሳቡን አርዕስትና የገንዘቡ ብዛት በመደመር በቀላሉ የሚመዘገብበት ዘዴ ነው::

በዚህ ዘዴ ስህተቶች ሲፈጠሩ ለማግኘት ያዳግታል:: የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ከቅለቱ የተነሳ በተወሰነ ደረጃ ይህን ሲጠቀሙ የሚስተዋሉ በመሆናቸው በቀጣይ ሁሉም የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ነጠላ የሂሳብ አመዘጋገብ ዘዴ እንዳይጠቀሙ መምከርና ጥቅሙንና ጉዳቱን በደንብ ግንዛቤ ማስጨበጥ ያስፈልጋል::

ሰንጠረዥ 1 ነጠላ የሂሳብ አመዘጋገብ

| ቀን | ገለፃ | ሚዛን |
|---|---|---|
| ነሐሴ 4/2010 | ሲደመር የገቢ ሚዛን | 2500.00 |
| ነሐሴ 7/2010 | የሚሸጥ ዕቃ ግዥ | (1200.00) |
| ነሐሴ 10/2010 | የተሸጠ ዕቃ | 1500.00 |
| መስከረም 8/2011 | የአቅርቦት ዕቃ ግዥ | (150.00) |
| መስከረም 12/2011 | የኤሌክትሪክ ክፍያ | (120.00) |
| መስከረም 15/2011 | የመጨረሻ ሚዛን | 2530.00 |
| | | |

### 2. መንትያ የሂሳብ ምዝገባ ስርዓት

መንትያ ወይም ጥንድ የሂሳብ አመዘጋገብ ዘዴ ማለት የዴቢት ጠቅላላ የሂሳብ መጠን እና የክሬዲት የሂሳብ ልክ አንዱ ከሌላው ጋር እኩል እንዲሆን በሚያስችል አኳኋን የሚመዘገብበት ዘዴ ነው::

በዚህ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ማናቸውም የንግድ ክንውን ወይም ልውውጥ /transaction/ ሁሉ ቢያንስ የሁለት ነገሮች ንክኪ አለው::

ይኸውም አንዱ በመጨመር ሌላው በመቀነስ ነው፤ይህንንም በዴቢት እና በክሬዲት በመለየት እና በመመዝገብ የሁለቱም ድምር እኩል መሆኑን ማረጋገጥ ይኖርብናል፡፡ እኩል ማለት የሚያሳየው የድርጅቱ አጠቃላይ ንብረት ከዕዳና ካፒታል ድምር ጋር እኩል መሆኑን ነው፡፡ በዚህ መሰረት የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች መንትያ የሂሳብ አመዘጋገብ ዘዴን እንዲጠቀሙ ተገቢው ምክርና የድጋፍ አገልግሎት እንዲያገኙ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡

በአጠቃላይ መንትያ የሂሳብ መዝገብ አመዘጋገብ በሂሳብ መዝገብ ውስጥ ከዚህ በታች በሚመለከተው መልኩ መመዝገብ ይኖርበታል፡፡

ሰንጠረዥ 2 መንትያ የሂሳብ ምዝገባ ስርዓት

| ተ.ቁ | የሂሣብ ዋና መደብ | ሲጨምር | ሲቀንስ | መደበኛ ሚዛን |
|---|---|---|---|---|
| 1 | ሀብት /Asset/ | ዴቢት | ክሬዲት | ዴቢት |
| 2 | ዕዳ /Liability/ | ክሬዲት | ዴቢት | ክሬዲት |
| 3 | ካፒታል /Capital/ | ክሬዲት | ዴቢት | ክሬዲት |
| 4 | ገቢ /Revenue/ | ክሬዲት | ዴቢት | ክሬዲት |
| 5 | ወጪ /Expenses/ | ዴቢት | ክሬዲት | ዴቢት |

## 4.2 መሰረታዊ የሂሳብ አያያዝ ስርዓቶች እና አገልግሎታቸው

### 4.2.1 የሂሳብ አያያዝ መሰረቶች

የሂሳብ አያያዝ መሰረቶች፦

1. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ
2. አክሩራል ሂሳብ አያያዝ
3. የተሻሻለ የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ

ለዚህ ማሳያ ማኑዋል ለማሳየት እንዲረዳ ሁለቱን የሂሳብ መሠረቶች ለኢንተርፕራይዞች ሂሳብ አያያዝ በቂ በመሆኑ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡ ኢንተርፕራይዞች እንደ ንግድ እንቅስቃሲያቸው የሚወሰን ቢሆንም የበለጠ አክሩራል የሂሳብ አያያዝን እንዲከተሉ ማስገንዘብ ያስፈልጋል፡፡

1. የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ (cash Basis Accounting) ፡

የጥሬ ገንዘብ ሂሳብ አያያዝ በጥሬ ገንዘብ እንቅስቃሴ ላይ የተመሰረተ ሆኖ፣ አንድ የንግድ እቃ ወይም አገልግሎት ክስተት በገቢ የሚመዘገበው ገንዘብ ስንቀበል እና በወጪ ደግሞ ገንዘብ ስንከፍል ብቻ መሆኑ ነው፡፡ ይህም ማለት በዱቤ የምንሰበስበው ወይም የምንከፍለው

አይኖርም ማለት ነው፡፡

2. አክሩራል ሂሳብ አያያዝ (accrual base accounting):

በዚህ የሂሳብ አያያዝ መሰረት ገቢ በገቢነት ተይዞ የሚመዘገበው አገልግሎት ከተሰጠ ወይም የንግድ ዕቃ ለገዛው ግለሰብ (ተቋም) የባለቤትነት መብት ከተላለፈ በኂላ መሆኑ እና ወጪ በወጪነት የሚያዘው አገልግሎት ከተወሰደ በኃላ ወይም የንግድ ዕቃ ተግዝቶ ንብረት ክፍል ገቢ መደረጉ ሲረጋገጥ እና የባለቤትነት መብት ሲረከብ ነው፡፡

**ማስታወሻ፡-**

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች እንደ ንግድ እንቅስቃሴያቸው መጠንና ሁኔታ አሰራራቸውን የሚወሰን ሲሆን በዚህም መሰረት የሂሳብ አያያዝ መሰረቶች ውስጥ አኩራል የሂሳብ አያያዝን መከተል ቢችሉ በሚል እያስገነዘብናቸው መሄደ ያስፈልግል፡፡

## የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ /Bank Reconciliation/

በየወሩ ማጠናቀቂያ የባንክ ሂሳብ መግለጫ /Bank Statement/ ከባንክ ሊወሰድ ይገባል፡፡ ይህም የባንክ ሂሳብ መግለጫ የአገልግሎት መስጫ ተቋሙ/ኢንተርፕራይዙ/ ከሚይዘው የባንክ ሂሳብ ጋር በየወሩ እያናበቡ ማስታረቅ ይገባል፡፡

ለምሳሌ የባንክ አገልግሎት የሂሳብ መዝገብ ላይ ያልኖረ ወይም በሂሳብ መዝገብ ላይ ሰፍሮ በባንክ ላይ ያልተመዘገበ ከሆነ ባንክ ሂሳቡ መታረቅ አለበት፡፡ ለአብነትም የተከፈለ ቼክና ወደ ኢንተርፕራይዙ ባንክ ሂሳብ እንዲገባ ተልኮ ያልደረሰ ባንክ ገና ያልተመዘገበውን መጥቀስ ይቻላል፡፡ የገንዘብ እንቅስቃሴዎች በአጠቃላይ በአንድም በሌላም ምክንያት ከባንክ ጋር ልውውጥ ስለሚኖርባቸው በባንክ ያላቸው ሂሳብና የኢንተርፕራይዙ መዝገብ በየወሩ ማስታረቅ ይኖርብናል፡፡

የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ የሚከተለውን ቅርጽና ይዘት ይኖረዋል፡-

XX ኢንተርፕራይዝ

የባንክ ሂሳብ መግለጫ

የ------- ወር 20XX

| | | |
|---|---|---|
| የገንዘብ ሚዛን በባንክ ሂሳብ መግለጫ መሰረት | XX | |
| ሲደመር፡ | | |
| ሲቀነስ፡ ለባንክ ያልቀረበ ቼክ | XX | |
| ሲቀነስ፡ የደንበኛው ስህተት | XX | XX |
| የተስተካከለ ሚዛን | | XX |
| የገንዘብ ሚዛን በደንበኛው የሂሳብ መዝገብ መሰረት | | XX |
| ሲደመር፡ ቃል የተገባና የተገኘ ወለድ | | XX |
| ሲቀነስ፡ የባንክ አገልግሎት/ቼክ የተገዛበት | XX | XX |
| የተስተካከለ ሚዛን | | XX |

ምሳሌ፡- XX ሕ/ሽ/ማህበር በበጀት ዓመቱ መዝጊያ ያዘጋጀው የባንክ ማስታረቂያ የሚከተለው ነበር፡፡

- የካቲት 28/2008 ዓ.ም የባንክ ሂሳብ መግለጫ የመጨረሻ ሚዛን የሚያሳየው ብር 300,000.00 ሲሆን የኢንተርፕራይዙ መዝገብ ላይ የሚታየው ብር 260,900.00 ነው፡፡
- ባንክ ሂሳብ መግለጫው ብር 100.00 የአገልግሎት ክፍያ አለው፡፡
- የባንክ መግለጫው ከወለድ የተገኘ ገቢ ብር 20.00
- ኢንተርፕራይዙ ብር 50,000.00 ቼክ ኢሹ አደረገ፤ነገር ግን ባንኩ አልመዘገበውም
- ኢንተርፕራይዙ ብር 20,000.00 ባንክ ቢያስገባም በባንክ ሂሳብ መግለጫው ላይ አይታይም
- ብር 470.00 ለቢሮ አቅርቦት ቢውልም በገንዘብ መክፈያ መዝገብ ላይ ሪፖርት የተደረገው ብር 370.00 ነው፡፡
- ብር 9,800.00 በዱቤ የወሰዱት ደንበኞች የተሰበሰበ ነው፡፡
- ኢንተርፕራይዙ ብር 520.00 NSF

በዚህ መሰረት የባንኩና የኢንተርፕራይዙ መዝገብ ከዚህ በታች እንደሚመለከተው የማስታረቅ ስራ ተከናውኗል::

XX ሕ/ሽ/ማህበር

የባንክ ሂሳብ ማስታረቂያ

የካቲት 28/2008

| | | | |
|---|---|---|---|
| በባንክ ሂሳብ መግለጫ መሰረት | | | 300,000.00 |
| + ዲፖዚት ኢንትራንዚት | 20,000.00 | | |
| ሲቀነስ ለባንክ ያልቀረበ ቼክ | 50,000.00 | | -30,000.00 |
| ተስተካከለ የባንክ ሚዛን | | | 270,000.00 |
| በኢንተርፕራይዙ የሂሳብ መዝገብ መሰረት የመጨረሻ ሚዛን | | | 260,900.00 |
| ቃል የተገባ እና የተከፈለ | | 9,800.00 | |
| የተገኘ ወለድ | | 20.00 | 9,820.00 |
| | | | 270,720.00 |
| ስህተትየሆነ ቼክ | 100.00 | | |
| NSF | 520.00 | | |
| የባንኩ አገልግሎት ክፍያ | 100.00 | | 720.00 |
| የኢንተርፕራይዙ የሂሳብ መዝገብ የተስተካከለ ሚዛን | | | 270,000.00 |

## 4.3 የሂሳብ አርዕስቶች እና መለያ ቁጥሮች

### 4.3.1 የሂሳብ አርዕስቶች

የተለያዩ ሂሳቦችን እንደ ባህሪያቸው በዋና አርዕስት፣በንዑስ አርዕስቶችና በዝርዝር አርዕስቶች መድበን ለእያንዳንዳቸው የተለየ ቁጥር ወይም ምድብ /ኮድ/ ሰጥቶ መስራት የሂሳብ አያያዙን ዘመናዊና ቀልጣፋ ለማድረግ ከማስቻሉም ባሻገር ወቅታዊና አስተማማኝ የሂሳብ መረጃዎችን በስርዓት ለመያዝ፣ የሂሳብ ሪፖርቶችንና መግለጫዎችን በቀላሉ ለማዘጋጀት ይጠቅማል::

በዚህም መሰረት የሂሳብ አርዕስቶች እና መለያ ቁጥሮች በዋና የሂሳብ አርዕስቶች፣ በንዑሳን የሂሳብ አርዕስቶችና በዝርዝር የሂሳብ አርዕስቶች ሊመደቡና የመለያ ቁጥሮች ሊሰጣቸው ይችላሉ::

**የሂሳብ አርዕስት** /classification of Accounts/ :- ማለት እያንዳንዱ ሂሳብ በሂሳብ ቋት / ledger/ ውስጥ በሚመዘገብበት ወቅት የሚሰጠው ስያሜ የያዘ መለያ ነው::

የሂሳብ አርዕስቶች የሚከተሉትን 5 ዋና ዋና አርዕስቶች መያዝ ይኖርባቸዋል። እነርሱም ሀብት፣ዕዳ፣አንጡራ ሀብት፣ገቢ እና ወጪ በማለት በቅደም ተከተል እናስቀምጣቸዋለን።

1. የሀብት ዋና መደብ /Assets/ ፡-

ሀብት ማለት፡- አንድ ኢንተርፕራይዝ የራሱ የሆነ ወይም የሚቆጣጠረው የወደፊት ጥቅም ያስገኛል የሚል ተስፋ ያለው መዋዕለ ነዋይ እሴት ነው ። ሀብቶች በኢንተርፕራይዙ የሂሳብ መዝገብ ላይ ሪፖርት የተደረጉ እና የተገዙ ወይም በኢንተርፕራይዙ የተፈጠሩ፤ የኢንተርፕራይዙን ዋጋ የሚጨምሩ እና ስራዎች በሚከናወኑበት ጊዜ ጥቅም የሚያስገኙ ናቸው። ሀብት በውስጡ ሁለት ክፍሎች ይኖሩታል እነዚህም ፡-

ተንቀሳቃሽ /ጊዚያዊ/ ሀብት፡- ከአንድ ዓመት በታች በሆነ ጊዜ ውስጥ ለተቋሙ(ለኢንተርፕራይዙ) መደበኛ ስራዎች አገልግሎት ላይ የሚውሉ ናቸው። ለምሳሌ ተሰብሳቢ፣ አቅርቦት፣ ኢንቬንተሪ(ክምችት) የመሳሰሉትን መጥቀስ ይቻላል።

ቋሚ ሀብት፡- ለረጅም ጊዜ/ ከአንድ ዓመት/ በላይ አገልግሎት ሊሰጡ የሚችሉ ዋጋቸው ከብር 1000.00 በላይ የሆነ የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች ማለት ነው። ነገር ግን ዋጋቸው ከአንድ ሺህ ብር ዝቅ ያለና ከአንድ ዓመት በላይ አገልግሎት ያላቸው ንብረቶችን በንብረትነት ተመዝግበው የእርጅና ተቀናሽ ማስላት ስለማይቻል በልዩ የንብረት መቆጣጠሪያ ተይዘው አገልግሎት መስጠት ሲያቆሙ በኢንተርፕራይዙ የአሰራር ስርአት መሰረት በማስወገድ በወጪ ተይዘው ሪፖርት ይደረጋል።

2. የዕዳ ዋና መደብ /Liabllity/ ፡-

ዕዳ፡- ኢንተርፕራይዙ ስራውን ለማስፋፋት ከተለያዩ ግለሰቦችና ድርጅቶች በውል የተበደረው እና በዱቤ የገዛው እቃን በሙሉ ያካትታል። ዕዳን ከጊዜ አንፃር በመመልከት በሁለት ዓይነት መልኩ ከፍለን ልንመለከታቸው/ልንመዘግባቸው እንችላለን።

1. የአጭር ጊዜ ዕዳ፡- ማለት የተከፋይ ዕዳው ከአንድ ዓመት በታች የሆነና ለአበዳሪው አካል በአጭር ጊዜ ውስጥ የምንከፍለው ነው።
2. የረጅም ጊዜ ዕዳ፡- ይህ የዕዳ ዓይነት ከአንድ ዓመት በላይ ለአበዳሪው አካል የሚከፈል የጊዜ ርዝማኔ ያለው ሲሆን አከፋፈሉም በውሉ መሰረት ይሆናል። በአጠቃላይ ብድሮቹ/ ዕዳው በወለድ/ ያለ ወለድ/ ሊሆን ይችላል።

ለምሳሌ፡- ቴውዶርስ ኢንተርፕራይዝ ከአዲስ ብድር ተቋም ብር 200,000.00 የሁለት ወራት የእፎይታ ጊዜ ተሰጥቶት በሁለት ዓመት ጊዜ ውስጥ ተጠናቆ የሚከፍልና 8% ወለድ ታሳቢ የተደረገ ብድር ወሰደ።

ይህ ብድር የረጅም ጊዜ ዕዳ በሚለው ውስጥ የሚካተት ሲሆን ኢንተርፕራይዙ በመዝገቡ ላይ በረጅም ጊዜ የሚከፈል መሆኑን አውቆ በውሉ መሰረት ግዜውን ጠብቆ ብድሩን እየመለሰ በመዝገብ ላይ በአግባቡ መመዝገብ ይገባዋል።

3. የአንጡር ሀብት ዋና መደብ /Capital/ ፦

አንጡራ ሀብት፦ ከጠቅላላው ከኢንተርፕራይዙ ገንዘብና ንብረት ለአበዳሪዎች ድርሻ እና ሌሎች እዳዎች ከተቀነሰ በኋላ ያለው ቀሪ ሂሳብ ማለት ነው። አንጡራ ሀብት በሶስት መንገድ መልኩ ከፍለን ማየት እንችላለን እነርሱም፦

የሚዘጋ /በቀጣይ ዓመት የማይተላለፍ/ የካፒታል ዓይነት፦ ይህ የካፒታል ዓይነት የበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ የሚዘጋ ሲሆን ለቀጣይ ዓመት የማይሸጋገር ነው። ለምሳሌ፦ የትርፍ ክፍፍል እና ዊዝድሮዋል

የማይዘጋ /በቀጣይ ዓመት የሚተላለፍ/ ካፒታል፦ ይህ የካፒታል ዓይነት ኢንተርፕራይዙ ለስራ ማስኪያጀነት ያስመዘገበው ወይም ተጨማሪ መዋዕለ ነዋይ ያፈሰሰበት ሲሆን በዓመቱ መጨረሻ ላይ ሳይዘጋ ለሚቀጥለው በጀት ዓመት የሚሸጋገር የካፒታል ዓይነት ነው፤ ነገር ግን ካፒታሉ በትርፍ (በኪሳራ) ሊጨምር /ሊቀንስ ይችላል።

የትርፍ ተቀማጭ (Retained Earning)፦ ይህ የካፒታል ዓይነት ከትርፍ ክፍፍል በኋላ የሚገኝና አጠቃላይ የካፒታል መጠን የሚያሳድግ ይሆናል።

1. የገቢ ዋና መደብ /Revenue/፦

ገቢ፦ ኢንተርፕራይዝ የተለያዩ አገልግሎቶችን ከሰጠ በኋላ የሚያገኘው የአገልግሎት ክፍያ ማለት ነው። ለምሳሌ፦ ሽያጭ

2. የወጪ ዋና መደብ /Expenses/

ወጪ፦ ኢንተርፕራይዙ የተቋቋመበትን አገልግሎት በመስጠት ሂደት ውስጥ በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚፈፀም ክፍያ ማለት ነው። እነዚህ ዋና ዋና መደቦች እያንዳንዳቸው በሥራቸው በርካታ የሂሣብ ርዕሶች ይኖሯቸዋል።

## 4.3.2 የሂሳብ መለያ ቁጥር

የሂሳብ መለያ ቁጥር ማለት እያንዳንዱ የሂሳብ አርዕስት ስር ያሉ በቀላሉ ለመለየት እንዲቻል የሚሰጥ መለያ ቁጥር ነው።

ዋና መደቦችን፤ የሂሣብ ርዕሶችንና የሂሳብ መለያ ቁጥሮችን በቅደም ተከተል በዝርዝር የያዘ ሠንጠረዥ የሂሣብ ስም እና መለያ ቁጥር (Chart of account) በመባል ይታወቃል።

ሰንጠረዥ 3 የሂሳብ ስም እና መለያ ቁጥሮች

የ----------ጥ/አ/ኢ/ህ/ሽ/ማህበር

የሂሳብ ስም እና መለያ ቁጥር (Chart of account)

| የሂሣብ መደቦችና ርዕሶቻቸው | የሂሣብ መለያ ቁጥር | የሂሣብ መደቦችና ርዕሶቻቸው | የሂሣብ መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|
| 1. ሀብት/Assets/ | | 4. ገቢ /Revenue/ | |
| ጥሬ ገንዘብ | 1100 | ሽያጭ ገቢ | 4100 |
| ያልተሸጠ ዕቃ | 1101 | ልዩ ልዩ | 4101 |
| ተሰብሳቢ ሂሣብ | 1102 | 5. ግኽ/C.G.S | |
| የፅዳት ዕቃ | 1103 | ግኽ | 5100 |
| የፅዳት መሣሪያ | 1104 | 6. ወጪ /Expenses/ | |
| ቅድሚያ ክፍያ | 1105 | የቤት ኪራይ ወጭ | 6100 |
| ቋሚ ዕቃ | 1106 | የፍቃድ ማሳደሻ ወጭ | 6101 |
| 2. ዕዳ /Liability/ | | የደመወዝ ወጪ | 6102 |
| ተከፋይ ሂሣብ ለገቢዎች ከትርፍ | 2100 | የፅዳት ዕቃ ወጪ | 6103 |
| የባንክ ብድር | 2101 | የጽሕፈት መሣሪያ ወጪ | 6104 |
| ከሻት የተሰበሰበ ተከፋይ | 2102 | የጉልበት ዋጋ ወጪ | 6105 |
| 3. አንጡራ ሀብት /Capital/ | | የባንክ ወለድ ወጪ | 6106 |
| ህ/ሽ/ማህበር ካፒታል | 3100 | የጥገና ወጪ | 6107 |
| ዕጣ /Share/ | 3101 | የእርጅና ቅናሽ ወጪ | 6108 |
| ስጦታ /Donation/ | 3102 | ልዩ ልዩ ወጪ | 6109 |
| መጠባበቂያ /Reseve Fund/ | 3103 | | |

## 4.4 መሰረታዊ የሂሳብ አያያዝ ቀመር እና የሂሳብ መነሻ ሚዛን

### 4.4.1 መሰረታዊ የሂሳብ አያያዝ ቀመር

በሒሳብ አያያዝ የሒሳቦችና የሒሳብ አርዕስቶች ግንኙነት የሚገለጽበት ቀመር የሂሳብ አያያዝ ቀመር /accounting equation/ ይባላል ::ይኸውም ሀብት እኩል ይሆናል ዕዳ ሲደመር አንጡራ ሀብት (ካፒታል) በመባል ይታወቃል:: በሌላ በኩል ይህ ቀመር የሀብት እና ዕዳ ቀመር በመባል ይታወቃል:: መሰረታዊ የሂሳብ አያያዝ ቀመር ለመንትያ አመዘጋገብ ስርዓት መሰረት ነው::

ሀብት = ዕዳ + አንጡራ ሀብት

በዚህም መሰረት የሂሳብ ቀመሩን ተከትለን የሂሳብ አርዕስቶቹን በማስገባት ሲተነተን ፡-

ሰንጠረዥ 4 በሂሳብ ቀመር ውስጥ በምሳሌነት የሚገቡ የሂሳብ አርዕስቶች

| ሀብት | ዕዳ | የተጣራ ሀብት |
|---|---|---|
| ጥሬ ገንዘብ | ለድርጅት የሚከፈል | በሀብትና በዕዳ መካከል ያለው ልዩነት |
| ተሰብሳቢ ሂሳብ | ለመንግስት የሚከፈል | ዕጣ፣ |
| ተንቀሳቃሽና ቋሚ ዕቃ | ለሰራተኛ ያልተከፈለ ደሞዝ | መጠባበቂያ፣ ስጦታ…ወዘተ |
| በመጋዘን ያለ ጥሬ ዕቃ ወዘተ | ለአገልግሎት ያልተከፈለ ዕዳ | |
| | / ስልክ መብራት/ ወዘተ | |

## 4.4.2 የሒሳብ መነሻ ሚዛን /opening balance/

አንድ ነባር ወይም ጀማሪ ኢንተርፕራይዝ ወደ ስራ ከመገባቱ በፊት ለበጀት ዓመቱ ወይም ለመጀመርያ ግዜ በመነሻነት የሚከፈት የሒሳብ አይነት ነው። የሒሳብ መነሻ ሚዛን ኢንተርፕራይዞቹ ከግል፣ ከብድር እንዲሁም በስጦታ ሊያገኙት ይችላሉ። ይህም፡-

ሀ. ኢንተርፕራይዙ ያለው ጠቅላላ ሀብት

ለ. ኢንተርፕራይዙ ያለበት ጠቅላላ ዕዳ

ሐ. ኢንተርፕራይዙ ያለው የተጣራ ሀብት አጠቃሎ የሚይዝ ሲሆን በሁለቱም ጎን ያሉት ሚዛኖች እኩል መምጣት ይኖርባቸዋል።

ለጀማሪ ኢንተርፕራይዞች በመጀመርያ የሂሳብ መዝገብ ከመጀመራቸው በፊት የተነሱበትን ለማሳየት እንዲቻል ይህንን የሒሳብ መነሻ ሚዛን የሀብት እና ዕዳ መግለጫ በመክፈት መሰረታዊ የሂሳብ አያያዝ ቀመር ተጠቅመው ማረጋገጥ ይገባል።

# 4.5 የሂሳብ አያያዝ ሑደት

የሂሳብ አያያዝ ሑደት ማለት አንድ ሂሳብ የሚያልፈበት ሂደት ሲሆን፤ የሚከተሉት ቅደም ተከተል ይይዛል

1. ክስተት /Occurrence/Analysis Accounting Events/

ክስተት የሂሣብ አያያዝ ዑደት የመጀመሪያ ክፍል ሲሆን ትርጉሙም ከድርጅቱ (ከኢንተርፕራይዙ) የሥራ እንቅስቃሴ ጋር በተያያዘ በገንዘብ ሊገለፅ የሚችል የመሸጥ፣ የመለወጥ እና የመግዛት ክንውን መፈጠር ማለት ነው።

## 2. የሰነድ ዝግጅት /Document Preparation/

አንድ ኢንተርፕራይዝ በስራው እንቅስቃሴ ምክንያት የሚፈጠርን የገንዘብ አሰባሰብና ክፍያ እንዲሁም ያለገንዘብ የሚደረግ እንቅስቃሴ (ገቢና ወጪ) በማስረጃነት መዝግቦ ለመያዝ የሚያስችል ሰነድ ማዘጋጀት ማለት ነው።

ሰነዶች በአጠቃቀማቸውና በአያያዛቸው በሁለት ይከፈላሉ፤-

1. ጊዚያዊ ሰነድ
2. ቋሚ ሰነድ

1. ጊዚያዊ ሰነድ፡- ማለት በአንድ ዓመትና ከዚያ በታች ለሆነ ጊዜ ለይተን ለመረጃነት የምንጠቀምባቸው ሠነዶች ናቸው።

2. ቋሚ ሰነድ፡- ከአንድ ዓመት በላይና እስከ አስር ዓመት ለሆነ ጊዜ ለይተን ለመረጃነት የምናስቀምጣቸው ናቸው።

ስራ አመራሩ የሂሳብ ሰነዶች በጥንቃቄ የሚቀመጡበትን ሁኔታዎች ማሟላትና ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

### መሰረታዊ የሂሳብ ሰነዶች የሚባሉት፤

1. የገቢ መሰብሰቢያ ደረሰኝ፣
   - ✓ የውስጥ ገቢ ማሰባሰቢያ
2. የሽያጭ ደረሰኝ /sales invoice/፣
   - ✓ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ/cash sales invoice/
   - ✓ የዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ/Credit Sales invoice/
3. የወጪ ማዘዢያ ደረሰኝ፣
4. የእቃ ገቢና ወጪ ደረሰኝ፣
5. የቅድሚያ ገንዘብ መቀበያ/መክፈያ/ወይም ተንጠልጣይ ሂሳብ። የመሳሰሉት ሲሆኑ

### መሰረታዊ የሂሳብ ቅፃች

- ፋክቱር ለሌላቸው ግለሰቦች መክፈያ፣
- የደመወዝ መክፈያ፣
- የውሎ አበል እና የትራንስፖርት መክፈያ፣
- የቅድመ ገንዘብ መጠየቂያ እና መክፈያ፣
- የብድር እና የቤት ክራይ ስምምነት ውል፣

ለምሳሌ፡- ከዚህ በታች በተጨማሪ እሴት ታክስ ተመዝጋቢ በሆነ ኢንተርፕራይዝ የተዘጋጀ ደረሰኝ (ሰንጠረዥ 5)

# ሰናይ የግብዓት አቅራቢ የህ/ሽ/ማህበር

ስልክ 00000000/00001000 ቀን 15/06/09

የደ/ቁ 001

## የተጨማሪ እሴት ታክስ የእጅ በእጅ ሽያጭ ደረሰኝ

## VALUE ADDED TAX CASH SALES INVOICE

ከ ሰናይ የግብዓት አቅራቢ የህ/ሽ/ማህበር ለ ---------------------------------

አድራሻ XX ክ/ከተማ XX የቤ/ቁ XX አድራሻ XX ክ/ከተማ XX
የቤ/ቁ XX

የታ. ከፋይ መ/ቁ XXXXX የታ.ከፋይ መ/ቁ XXXXXXXXXX

የሻጭ የተ.እ. ታ ቁጥር ------------------- የገዢ የተ.እ.ታ ቁጥር XXXXX

የተመዘገበበት ቀን 25/05/09 ዓ.ም የተመዘገበበት ቀን XX /XX/ XXXX

ዕቃው የተሰጠበት ቀን XX /XX/ XXXX

| ቁጥር | የአገልግሎት ዓይነት | መለኪያ | ብዛት | የአንዱ ዋጋ | | ጠቅላላ ዋጋ | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | ቁልፎች | በቁጥር | 10 | 34 | 78 | 347 | 80 |
| 2 | አረ.ኤች.ኤስ | በቁጥር | 2 | 130 | 40 | 260 | 80 |
| | | | | | | | |
| | | ጠቅላላ ድምር | | | | 608 | 69 |
| | | ተ.እ.ታክስ | | | | 91 | 31 |
| | | | | | | 700 | 0 |

| የገንዘቡ ልክ በፊደል | ሰባት መቶ ብር ብቻ |
|---|---|

የክፍያ ሁኔታ በጥሬ ገንዘብ በቼክ የቼክ ቁጥር --------------

ስርጭት 1ኛ ኮፒ ለከፋይ 2ኛ ኮፒ ለሂሳብ ክፍል 3ኛ ኮፒ ከጥራዙ ላይ ቀሪ

## የሰነድ አያያዝ

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች የተለያዩ የሂሳብ ሰነዶችን በማሳተም አገልግሎት ላይ ያውላሉ፡፡ እነዚህ ሰነዶች አገልግሎት የሰጡ፣ በመስጠት ላይ ያሉና አገልግሎት ላይ ያልዋሉ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡ ነገር ግን እነዚህ ሰነዶች የሂሳብ ምርመራን ጨምሮ ለተለያዩ ተግባራት በተለያዩ ጊዜ ሊፈለጉ ይችላሉ ስለሆነም ሰነዶቹ በጥንቃቄና ቅደም ተከተላቸውን ጠብቀው መያዝ ይኖርባቸዋል፡፡ እነዚህ ሰነዶች በገቢ መስሪያ ቤቶች በኩል እንዲታተሙ ፍቃድ ሲሰጣቸው ብቻ የሚታተሙ ይሆናል፡፡

የሂሳብ ሰነዶች በተለያዩ ምክንያቶች ከጠፉ የስራ አመራር ኮሚቴው የጠፉ ደረሰኞችን ብዛትና ተከታታይ ቁጥሮችን በመለየት በአስቸኳይ ህጋዊ እርምጃዎችን በመውሰድ ክትትል ማድረግ ይኖርበታል፡፡ በተለይም በአካባቢው ፖሊስና ለመገናኛ ዘዴዎች በማሳወቅ የጠፉት ሰነዶች በአጭበርባሪዎች ስራ ላይ እንዳይውሉ መከላከል ያስፈልጋል፡፡

## 3. መመዝገብ /Journalizing/

በመዝገብ መመዝገብ ማለት ማናቸውም የድርጅቱ ገንዘብ ነክ እንቅስቃሴዎች የሆኑት ክስተቶች ከመሠረታዊ ሰነዶች ማለትም ከገቢ መሰብሰቢያና ከወጭ ማዘዣ ደረሰኞች ወደ ድርጅቱ መዝገብ ወይም ጆርናል መመዝገብ ማለት ሲሆን፣

በሂሣብ አያያዝ ሕግ መሠረት ተቀባይነት ያላቸው የተለያዩ የሂሳብ መዛግብቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህም መካከል በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች ለማሳያነት ሶስቱን የሂሳብ መዝገቦች እንመለከታለን፡፡

ሀ. አጠቃላይ መዝገብ /General journal/፣

ለ) ልዩ መዝገብ /Special jounral/፣

ሐ) ጥምር መዝገብ (combination journal)

## ሀ. አጠቃላይ መዝገብ /General journal/

ይህ መዝገብ ማንኛውም ጠቅላላ የልውውጥ ክስተት የሚመዘገቡበት የመዝገብ ዓይነት ነው፡፡

## ለ. ልዩ መዝገብ /Special Journal

የድርጅቱ የሥራ እንቅስቃሴ ሰፊ እና ውስብስብ እየሆነ በሄደ ቁጥር አንዳንድ የሂሣብ ርዕሶችን በአጠቃላይ መዝገብ መመዝገቡ ድግግሞሽ የሚበዛበት እና ለክትትልም አመቺ የማይሆንበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡ በዚህ ጊዜ ድግግሞሽ የሚበዛበትን እና የተለየ ቁጥጥር የሚያስፈልገውን የሂሣብ ርዕስ አምድ የሚይዝ ልዩ መዝገብ ማዘጋጀት ጊዜን እና ንብረትን የሚቆጥብ በመሆኑ የተሻለ እና ተመራጭ ይሆናል፡፡

**ለምሳሌ**

- ✓ የገንዘብ ገቢ መዝገብ /Cash receipt Journal/
- ✓ የገንዘብ ወጪ መዝገብ /Cash Payment Journal/
- ✓ የጥሬ ገንዘብ መዝገብ፡-በእጅ እና በባንክ /Cash book & Cash bank/
- ✓ የግዢ መዝገብ/Purchase Journal፡-የዱቤ እና የእጅ በእጅ ግዢ /credit& on Cash Purchase Journal/
- ✓ የሽያጭ መዝገብ/sales Journal፡-የዱቤ እና የእጅ በእጅ ሽያጭ /credit& on Cash sales Journal/.

## ሐ. ጥምር መዝገብ (combination journal)

የጥምር መዝገብ (combination journal) አጠቃላይ እና ልዩ መዝገብ በአንድ ላይ በየርዕሳቸው አካቶ የሚይዝና በአንድ መዝገብ ላይ ተካተው የሚመዘገቡበት ነው። የጥምር መዝገብ በአብዛኛው የጥቃቅንና አነስተኛ እንዲጠቀሙበት ቢደረግ ለመዛግብት የሚወጣውን ወጪ ከመቀነሱ ባሻገር የምዝገባ ስራውን የሚያቀል በመሆኑ እንዲጠቀሙበት ይመከራል።

**ለምሳሌ፡-** ዋው የሕ/ሽ/ማህበር መስከረም 2/2010 ዓ.ም በሁለት ጓደኞሞች እኩል በብር 75,000.00 በማዋጣት በአገልግሎት ዘርፍ ተቋቋሙ።

| ሀብት | = | ዕዳ | + | የባለቤቶቹ አንጡራ ሀብት |
|---|---|---|---|---|
| ገንዘብ | | | | የዋው አንጡራ ሀብት |
| 150,000 | | | | 150,000 |

ይህ ልውውጥ በሁለቱም ጎን ተመሳሳይ የሆነ ውጤት ሲኖረው በሀብት በኩል ገንዘብ ሲጨምር በአንጡራ ሀብት በኩል ደግሞ የማህበሩ ካፒታል ያድጋል ማለት ነው። ስለሆነም ይህ ምዝገባ ላይ የሚታየው የማህበሩ ካፒታል ሆነ ገንዘብ የማህበሩ ትርፍ (ሌላ ገቢ) ሳይሆን ለማህበሩ ማቋቋሚያ የሚሆነው አንጡራ ሀብት መሆኑን መገንዘብ ይኖርብናል።

በጥምር መዝገብ ሲሰፍር እንደሚከተለው ይሆናል።

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ገንዘብ በእጅ | ገንዘብ በባንክ | ንብረት | ተሰብሳቢ | የፅ/መሳርያ | ቫት | ቋሚ ዕቃ | ዕዳ | አንጡራ ሀብት | ሽያጭ | ወጪዎች |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 2/1/2010 | | | | 150,000.00 | | | | | | | 150,000.00 | | |
| | | | | | | | | | | | | | |

## 4. ወደ ቋት ማስተላለፍ /Posting to ledger/

የሂሣብ ቋት የራሱ ባሕሪ ያለው የንብረት፣ የዕዳ፣ የካፒታል፣ የገቢና የወጪ ዓይነት ለየብቻ በሂሣብ ርዕሱ ተለይቶ የሚያዝበት መዝገብ ማለት ነው። በአጠቃላይ፣ በልዩ መዝገብ እና በጥምር መዝገብ የተመዘገበው እያንዳንዱ የገቢና የወጪ ሂሣብ ርዕስ ለየብቻ ወደ

ተከፈተለት የሂሣብ ቋት እየተላለፈ ይሰበሰባል:: ይህ ከአጠቃላይ ወይም ከልዩ መዝገብ ወደ ቋት የማስተላለፍ ሂደት ፖስቲንግ ወይም የማወራረስ ሂደት ይባላል:: በአጠቃላይ መዝገብ የተመዘገበ ሂሳብ በየዕለቱ ወደሌጀር መተላለፍ ያለበት ሲሆን በልዩ መዝገብና በጥምር መዝገብ የሚመዘገቡ ከሆነ ሂሳባቸው በእያንዳንዱ የሂሳብ ስም ስለተመዘገበ የወሩ ማጠቃለያ ድምርን ወደ ሂሳብ ቋት ማስተላለፍ ይቻላል::

የሂሣብ ቋት የቀን፣ መግለጫ፣ የማጣቀሻ፣የሂሳብ እንቅስቃሴው የሚታይበት /ዴቢት ክሬዲት/ እንዲሁም የሚዛን ዴቢት ክሬዲት አምዶች ይኖሩታል::

## ተቀፅላ ቋት /Subsdiary Ledger/

መቆጣጠሪያ/controlling ledger/ ድርጅቱ ከሁሉም ደንበኞች ምን ያህል እንደሚያሰባስብና እንዲሁም ለአበዳሪዎቹ ምን ያህል እንደሚከፈል ጥቅል መጠኑን የሚያሳይ ሲሆን ተቀፅላ ቋት ግን ከማን ምን ያህል መሰብሰብ እንዳለበትና ለማን ምን መከፈል እንዳለበት የሚያሳይ በየደንበኛው ስምና አድራሻ በተናጠል የሚዘጋጅ የቋት ዓይነት ነው::ይህ ቋት እንደ አስፈላጊነቱ ይዘጋጃል::

**የተሰብሳቢ ተቀፅላ ቋት ምሳሌ:-**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| **ስም**፡- ወንድሙ አብርሀም<br>**አድራሻ**፡- አዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ<br>**ልዩ ቦታ**፡- ጎጃም በረንዳ | | | | የአካውንት ቁጥር 102 |
| ቀን | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
| 02/ 02/ 2010 | 055 | 150,000.00 | | 150,000.00 |

## 5. ማስተካከያ ያልተሰራለት የሂሳብ መሞከርያ ሚዛን/ማመዛዘኛ /unadjusted trial balance

የሂሳብ መሞከርያ ሚዛን ማለት ቋት ወይም ሌጀር ላይ የሚገኘው የመጨረሻ ሚዛን/Running balance/ በሙሉ ተጠቃለው ቋቱ ላይ የሚገኘውን ስማቸውን እንደያዙ በቅደም ተከተል በመቀመጥ አጠቃላይ የሂሳቡን ትክክለኛነት የምናረጋግጥበት የመግለጫ ዓይነት ነው::

እያንዳንዱ የሂሣብ ርዕስ በየግል ቋቱ ላይ የሚኖረው የመጨረሻ ሚዛን በዴቢትና በክሬዲት ተለይቶ ከተመዘገበ በኋላ የሁለቱም ጎን ምዝገባ ጠቅላላ ድምር እኩል መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዳ ማመዛዘኛ ነው::

## 6. የሂሣብ ማስተካከያ ምዝገባ እና ወደ ቋት ማስተላለፍ /Adjusting entries and Posting/

በአብዛኛው ለትርፍ በተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች በበጀት ዘመኑ የሥራ ሂደት ውስጥ ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው የገቢ ወይም የወጪ ክስተቶች መፈጠር አይቀሬ ነው:: ማስተካከያ ምዝገባ

የሚያስፈልጋቸው ሂሳቦች ለምሳሌ፤

- በመጋዘን ያሉ እቃዎች/ Inventoris/
- አስቀድሞ የተሰበሰበ ገቢ /Deferred Revenu/Unearned/ ምሳሌ፤የቤት ኪራይ ክፍያ ፤የኢንሹራንስ ክፍያ የመሳሰሉት፡፡
- ያልተመዘገቡ ገቢዎች ወይም ወጪዎች/unrecorded expens or Revenu/ ምሳሌ፤ወለድ/interst
- የቅድሚያ ሃብት ምዝገባዎችን በሀብትና ወጪ መለየት/Identification of Asset
- የእርጅና ተቀናሽ /Depreciation/
- የቋሚ እቃዎችን ማስወገድ/Removing plant Assets/
- ጉድለት ያሳዩ ሽያጮች /Shortage of sales/

በምሳሌ 1፡- ላይ ለማየት አንድ ኢንተርፕራይዝ በዓመት ውስጥ ጥቅም ላይ ለማዋል የ500 ብር የጽዳት መገልገያ መሳሪያዎች ገዝቷል፡፡

በዓመቱ ማብቂያ ላይ ግን የ100 ብር የጽዳት እቃ ብቻ እንደቀረው የቆጠራ ሪፖርቱ ያረጋግጣል፡፡ ስለሆነም አስቀድሞ ሲገዛ፡-

የጽዳት እቃዎች...................... 500.00

ጥሬ ገንዘብ ............................ 500.00

በዓመቱ መጨረሻ ላይ ግን ለዘመኑ የተጠቀመበትን ብቻ በመለየት፡፡ ለሚቀጥለው በጀት ዓመት ምን ያህል ቀሪ እንዳለው ለማሳየት የሂሣብ ማስተካከያ ሊሰራለት ይገባል፡፡ በመሆኑም ጥቅም ላይ ለዋሉት የጽሕፈት መሳሪያዎች አመዘጋገቡም፡-

የጽዳት እቃ ወጪ …………….. 400.00

የጽዳት እቃዎች ………………… 400.00

ለምሳሌ 2፡- ቴዎዶር ኢንተርፕራይዝ በ30/10/2003ዓ.ም ለኢንተርፕራይዙ አገልግሎት የሚውል የብረት ማነጫ (lathe) ማሽን በብር 500,000.00 ከቫት ውጭ ገዛ፡፡ ስለሆነም ይህ ኢንተርፕራይዝ ንብረቱ ለ8ዓመት የሚያገለግል ሲሆን ስሌቱም እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

$$\frac{500,000}{8\text{ ዓመት}} \quad \text{ወይም} \quad 500,000.00*12.5\% = 62,500$$

በዚህም መሰረት የአንድ ዓመት የእርጅና ቅናሽ ብር 62,500 ሲሆን በ8 ዓመታት ውስጥ ያለውን ከዚህ በታች በሚከተለው ሰንጠረዥ በማስቀመጥ ማየት ይቻላል፡፡

| የዕቃው ብዛት | የተገዛበት ዋጋ | የዕርጅና ቅናሽ ዓመት | የዕርጅና ቅናሽ | የተጠራቀመ ዕርጅና ቅናሽ | የመዝገብ ዋጋ | አስተያየት |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 500,000 | 30/10/2003 | 62,500 | 62,500 | 437,500 | |
| | | 30/10/2004 | 62,500 | 125,000 | 375,000 | |
| | | 30/10/2005 | 62,500 | 187,500 | 312,500 | |
| | | 30/10/2006 | 62,500 | 250,000 | 250,000 | |
| | | 30/10/2007 | 62,500 | 312,500 | 187,500 | |
| | | 30/10/2008 | 62,500 | 375,000 | 125,000 | |
| | | 30/10/2009 | 62,500 | 437,500 | 62,500 | |
| | | 30/10/2010 | 62,500 | 500,000 | 0 | |

## 7. የሂሳብ መግለጫዎች ዝግጅት /Financial statement preparation/

በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ላይ የተሰሩ ሂሳቦች የሚጠቃለሉባቸው መግለጫዎች ሲሆኑ ዋና ዋናዎቹ ሶስት ናቸው:: እነዚህም :-

1. የትርፍና ኪሳራ መግለጫ/income statment/
2. የሀብትና ዕዳ መግለጫ/balance sheet/ እና
3. የገንዘብ ፍሰት /cash flow/

ምሳሌ:- የትርፍና ኪሳራ መግለጫ/income statement/ በተመለከተ በአንድ ኢንተርፕራይዝ ላይ የተሰራውን ለማሳያነት እንደሚከተለው ቀርቧል::

**ቃሉ እና ጓደኞቹ የህ/ሽ/ማህበር**

**የትርፍና ኪሳራ መግለጫ**

ከሀምሌ 1/2008 እስከ ሰኔ 30/2009 ዓ.ም

<u>ሽያጭ :</u>

ከምርት ሽያጭ/ ከአገልግሎት ሽያጭ --------------------------- 1260.86

የሽያጭ ድምር ---------------------------------------------------- 1260.86

ግዥ

በመጋዘን የነበረ (ሰኔ30/2009) ---------------------------- 0

ሲደመር ጠ/ግዥ ---------------------------------------------- 1660.83

ጠቅላላ /ለሽያጭ የቀረበ ------------------------------------- 1660.83

ሲቀነስ በመጋዘን የተቀጠረ -----------------------------------<u>761.73</u>

የተሸጠ ዕቃ የግዥ ዋጋ -------------------------------------- <u>899.10</u>

ከሽያጭ የተገኘ ጥቅል ትርፍ ---------------------------------------- 361.76

ሲቀነስ ወጭዎች ------------------------------------------------------ 389.56

ከታክስ በፊት የተገኘ ትርፍ ------------------------------------------- (27.8)

የሀብትና ዕዳ መግለጫ/balance sheet/ ምሳሌ ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርቧል።

**ቃሉ እና ጓደኞቹ ህ/ሽ/ማህበር**

**የሀብትና ዕዳ መግለጫ**

ሰኔ 30 ቀን 2009 ዓ/ም

ሀብት

ገንዘብ በእጅ -------------------- 3424.00

ገንዘብ በባንክ ------------------ 29700.00

ቫት ተመላሽ ------------------- 200.38

መሳርያ ---------------------- 120.00

ቀሚ ዕቃ ----------------------- 695.65

የተጠራቀመ ዕርጅና ቅናሽ ----------------------------------- 69.56

ተሰብሳቢ ሂሳብ ---------------- 450.00

የሚሸጥ ዕቃ ------------------- 761.73

ጠቅላላ ሀብት ------------------------------------------------ 35,351.76

ዕዳ

ብድር ----------------------------------------------------- 21310.00

የግብር ተከፋይ ------------------------------------------------ 0

ጠቅላላ ዕዳ ------------------------------------------------ 21310.00

ካፒታል

የአባላት መዋጮ ------------------------------------------ 14000.00

የ2009 ዓ.ም ኪሳራ -------------------------------------- (27.80)

ጠቅላላ ካፒታል ------------------------------------------ 13972.2

ጠቅላላ ዕዳና ካፒታል ------------------------------------ 35,351.76

## 8. ማጠናቀቂያ /የመዝጊያ ምዝገባ /Closing entries/

ጊዜያዊ ሂሳቦች ማለትም፡-ገቢ (Revenue) እና ወጪ (Expenses) አካውንቶች እንዲሁም የግል ወጪ (Drawing) እና የገቢ ማጠቃለያ (Income summary) አካውንቶች በበጀት ዓመቱ መጨረሻ ሂሳባቸው ተዘግቶ የተጣራ ውጤቱ ወደ አንጡራ ሃብት ሂሳብ ይተላለፋል።

ምሳሌ፡- የአንድ ኢንተርፕራይዝ በመጨረሻ (በበጀት ዓመቱ መዝጊያ) የሚከተሉትን የሂሳብ አርዕስቶች ሂሳብ ይዘጋል።

ገቢ ------------------ 1200.00

የገቢ ማጠቃለያ ------------- 1200.00

የገቢ ማጠቃለያ ------- 500.00

ወጪ -------------------------- 500.00

የገቢ ማጠቃለያ ------- 200.00

የግል ወጪ -------------------- 200.00

የገቢ ማጠቃለያ ------- 10,000.00

አንጡራ ሃብት--------------- 10,000.00

## 9. ድህረ መዝጊያ የሂሳብ መሞከሪያ ሚዛን/Post closing trial balance/

ድህረ መዝጊያ የሂሳብ መሞከሪያ ሚዛን ሊያሳይ የሚችለው በሚቀጥለው ዓመት የሚኖሩት ሀብት፣እዳ እና ካፒታል ነው። በአጠቃላይ የተዘጋው ሂሳብ በመጨረሻ ያለውን ሚዛን ትክክል መሆኑን የምናይበት የሂሳብ መሞከሪያ ሚዛን ድህረ መዝጊያ የሂሳብ መሞከሪያ ሚዛን ተብሎ ይጠራል።

## 10 የማመቻቻ ምዝገባ /Reversing entry/

የሂሳብ አመዘጋገብ ስርዓት ወጥነትን የሚያዛቡ አንዳንድ የሂሳብ ማስተካከያ ምዝገባዎች ሲያጋጥሙ በአዲሱ የሂሳብ ዘመን መጀመሪያ የማመቻቻ ምዝገባ በማካሄድ ወጥነቱ እንዲቀጥል ማድረግ ያስፈልጋል። ድህረ ምዝገባ ቀድሞ ተሰርቶ ከነበረው የማስተካከያ ምዝገባ ተቃራኒ ነው። ድህረ ምዝገባ የጄነራል ጆርናል ኢንትሪ ነው በእርሱ መጠቀም/መገልገል አንዱ አማራጭ የሂሳብ መዝገብ አያያዝ ሂደት ነው። ነገር ግን እንደ ሂሳብ መዝገብ አያያዝ ዑደት መታየት የለበትም።

በአጠቃላይ ከላይ የተጠቀሱት የሂሳብ አያያዝ ኡደቶች ፍሰታቸውን ከዚህ በታች በሚ ገኘው ስዕል ላይ መመልከት እንችላለን።

ሥዕል 1 ዘመናዊ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት ቅደም ተከተልን የሚያሳይ ሥዕል

<u>**የዘመናዊ ሂሳብ አያያዝ ስርዓት ቅደም ተከተል**</u>



# ክፍል አምስት፦ ታክስ /ግብር/

## 5.1 የታክስ ምንነት እና አስፈላጊነት

ታክስ ለመንግሥታዊ ተግባሮች ማከናወኛ የሚያስፈልግ ወጪ ለመሸፈን በሕግ መሠረት ከህብረተሰብ የሚሰበሰብ የገቢ ምንጭ ነው።

**የታክስ አስፈላጊነት፤**

- የመንግሥት የወጪ ፍላጎት ለማሟላት (የፋይናንስ ምንጭ)
- የገቢ ክፍፍል ለማድረግ
- የተረጋጋ የማይክሮ ኢኮኖሚ ለማስፈን
- ንግድና ኢንቨስትመንትን ለማበረታታት
- በጤና ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ማህበራዊ ጠቀሜታ የሌላቸውን ምርቶች አጠቃቀም ለመገደብ

## 5.2 የታክስ አወቃቀር

የታክስ አይነቶች በጥቅሉ ቀጥተኛ እና ቀጥተኛ ያልሆኑ ተብለው በሁለት ይመደበሉ።ቀጥተኛ ታክስ ገቢ ባገኘ የተፈጥሮ ወይም የህግ ሰውነት መብት ባለው ሰው ላይ የሚጣሉና ግብር የመክፈል ጫናው በቀጥታ ገቢውን ባመነጨው /ባገኘው ሰው ላይ የሚጣሉ የታክስ ዓይነቶች ናቸው። ዝርዝራቸው እና የማስከፈያ ምጣኔ ሰንጠረዦች በአዋጅ ቁጥር 979/2008 በወጣው መሰረት የሚከተሉት ናቸው፤

- የደመወዝ ገቢ ግብር ፡ሠንጠረዥ -ሀ
- የኪራይ ገቢ ግብር -ሠንጠረዥ-ለ
- የንግድ ሥራ ገቢ ግብር፡ ሠንጠረዥ-ሐ
- የእርሻ ሥራ ገቢ ግብር -በክልሎች የሚሰበሰብ
- ለሎች ሠንጠረዥ -መ ስር የምመደቡ ገቢዎች (ከተቀማጭ ገንዘብ ላይ ከሚከፈል ወለድ ገቢ ግብር ለመድህን በሚከፈል አረቦን ፣ ከስራ አመራር ክፍያ ወይም ከቴክኒክ አገልግሎት ክፍያ፣ ዕድል ሙከራ፣ ሮያሊቲ፣ አክስዮን የትርፍ ድርሻ፣ የካፒታል ንብረቶችን በማስተላለፍ የሚገኙ ጥቅሞች እና ንፋስ አመጣሽ ገቢ እና ሌሎች)

ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች በዕቃና አገልግሎቶች ላይ የሚጣሉ በሸማቹ ተከፍለውና በሻጮች ተሰብስበው ለታክስ ባለሥልጣን ገቢ የሚደረጉ ናቸው። ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች የሚከፈሉት ግዥ ሲፈፀም በመሆኑ የፍጆታ ታክሶች በመባልም ይታወቃሉ። የታክስ ጫናው የሚጣለው በተጠቃሚው ላይ በመሆኑና ግብር አስገቢዎቹ የታክስ ጫና ሰለሌለባቸው ቀጥተኛ ታክስ አይደሉም።

የሚከተሉት ቀጥታ ያልሆኑ ታክሶች ናቸው፤

የተጨማሪ እሴት ታክስ፣ ተርን ኦቨር ታክስ፣ ኤክሳይዝ ታክስ፣ የጉምሩክ ቀረጥ እና የቴምብር ቀረጥ

## ታክስ/ የግብር ከፋዮች ደረጃ

በገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 መሰረት ግብር ከፋዮች በአመታዊ ገቢያቸዉ መሰረት በሦስት ደረጃዎች ይከፈላሉ:: እነርሱም የደረጃ "ሀ"፣የደረጃ "ለ"፣ እና የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች ይባላሉ::

ሀ. የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች፡- የደረጃ "ሀ" ግብር ከፋዮች የሚባሉት ፡-

- ✓ ድርጅት
- ✓ ጠቅላላ አመታዊ ገቢው ብር 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) ወይም ከዚህ በላይ የሆነ ማንኛውም ግብር ከፋይ

ለ. የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች፡- የደረጃ "ለ" ግብር ከፋዮች የሚባለው ድርጅትን ሳይጨምር ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 1,000,000 (አንድ ሚሊዮን) የሚያንስ ነገር ግን ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ) እና ከዛ በላይ የሆነ፣

ሐ. የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋዮች፡- የደረጃ "ሐ" ግብር ከፋይ የሚባለው ድርጅትን ሳይጨምር ዓመታዊ ጠቅላላ ገቢው ከብር 500,000 (አምስት መቶ ሺ) የሚያንስ ማንኛውም ሰው ነው::

የደረጃ ሀ እና ለ ግብር ከፋዮች የሂሳብ አያያዝ እንዲተገብሩ የሚገደዱ ሲሆን ደረጃ ሐ በፍቃደኝነት የሂሳብ አያያዝ የሚተገበር ሲሆን በህጉ መሰረት ግን እንዲይዙ አይገደዱም::

ከላይ በግብር ከፋዮች ደረጃ የተቀመጠው እንዳለ ሆኖ የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በየትኛውም ደረጃ ላይ ቢሆኑ የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መተግበር ይገባቸዋል::

በገቢ ግብር አዋጁ በጥቃቅን ደረጃ ያሉ ኢንተርፕራይዞች ማህበርም ቢሆኑ ግብር የሚከፍሉት እንደ ግለሰብ እንጂ እንደ ድርጅት አለመሆኑ በአዋጅ ቁጥር 979/2008 በንግድ ድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ የሚሆነውን የንግድ ስራ ገቢ ግብር ምጣኔ 30 በመቶ በኢንተርፕራይዞች ላይ ተፈፃሚ እንዳይሆን በአዋጁ በክፍል አራት ውስጥ ምዕራፍ አንድ ንዑስ አንቀፅ 19/4 ላይ በግልፅ እንዲቀመጥ ተደርጓል:: በመሆኑም በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ይህንን ግንዛቤ ውስጥ በማስገባት ተግባራዊ እንዲደረግ መከታተል ያስፈልጋል::

## 5.3 የታክስ ሂሳብ አያያዝ (tax accounting)

### 5.3.1 የንግድ ሥራ ገቢ ታክስ/ግብር

በዚህ ማንዋል ማሳያ ሁሉንም ቀጥተኛ ታክሶችን ማሳየት ሰፊ ከመሆኑም በላይ ሁሉንም ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞችን የሚመለከት በቀጥታ ከሚመለከታቸው ውስጥ በማሳያነት አንድ ምሳሌ በዚህ ምዕራፍ መጨረሻ ላይ የተወሰደ ሲሆን ሌሎችን የግብር ዓይነቶች የገቢ ግብር አዋጅ ቁጥር 979/2008 ፣ደንብ ቁጥር 410/2009 እና ሌሎች መመርያዎችን በመጠቀም ግብርን በማስላት ማሳወቅ ይገባል፡፡

የንግድ ስራ ገቢ ማለት፡- ከመቀጠር የሚገኝ ገቢን ሳይጨምር ግብር ከፋዩ እቃዎችን በማስተላለፍ እንዲሁም አገልግሎቶችን በመስጠት የሚያገኘውን ገንዘብ መጠን ጨምሮ በግብር ዓመቱ ከንግድ ስራ ያገኘውን ጠቅላላ ገንዘብ መጠን ነው፡፡

የንግድ ሥራ ታክስን ለማስላት የታክስ መሰረት እና ምጣኔ ማወቅ ወሳኝ ነው፤ የታክስ መሰረት ማለት ታክስ የሚሰላበት ገቢ ሲሆን የታክስ ምጣኔ ደግሞ ታክሱን ለማስላት የተመደበ መቶኛ ነው ፡፡

በንግድ ሥራ ገቢ ላይ ተፈፃሚ የሚሆኑ ምጣኔዎች (አንቀጽ 19)

- በድርጅቶች ላይ ተፈፃሚ የሚሆነው የንግድ ሥራ ገቢ የግብር ምጣኔ ሰላሳ በመቶ (30%) ነው፡፡ ነገር ግን የጥቃቅን እና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በመንግስት ድጋፍ የተቋቋሙ በመሆናቸው በአዋጅ 979/2008 አንቀጽ 20 ላይ እንደተቀመጠው ግብር የሚከፍሉበት የታክስ ምጣኔ 0 - 35% ሆኖ በገቢ ምድብ ደረጃቸው የታክስ መሰረቱ በ 7 ተከፍለው ከዚህ በታች በሰንጠረዥ 5 እንደሚከተለው ቀርቧል ፡፡

ሠንጠረዥ 5 የንግድ ሥራ ገቢ ግብር ምጣኔዎች የሚያሳይ ሠንጠረዥ

| የንግድ ሥራ ገቢ | ግብር መጣኔ | ተቀናሽ |
|---|---|---|
| 0-7,200 | 0% | 0 |
| 7,201-19,800 | 10% | 720 |
| 19,801 - 38,400 | 15% | 1,710 |
| 38,401- 63,000 | 20% | 3,630 |
| 63,001- 93,600 | 25% | 6,780 |
| 93,601-130,800 | 30% | 11,460 |
| ከ 130,800 በላይ | 35% | 18,000 |

ግብር የሚከፈልበት የንግድ ስራ ገቢ የሚባለው በግብር ዓመቱ ከተገኘው ጠቅላላ የንግድ ስራ ገቢ ላይ በህግ የተፈቀዱ ወጪዎች ተቀንሰው የሚገኘው የተጣራ የገቢ መጠን ነው።

የአንድ ግብር ከፋይ ግብር የሚከፈልበት የግብር ዓመቱ ገቢ የሚወሰነው ግብር ከፋዩ በሂሳብ መግለጫዎቹ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች መሠረት በሚያዘጋጀው የትርፍና ኪሳራ ወይም የገቢ መግለጫ ላይ በመመስረት ይሆናል።

ምሳሌ 1፡- ዝናቡ ህይወትና ጓደኞቻቸው የህ/ሽ/ማህበር በ2011 የሂሳብ በጀት ዓመት በትርፍና ኪሳራ መግለጫቸው ላይ ብር 6,500.00 የተጣራ ትርፍ መኖሩን በሂሳብ መግለጫቸው ላይ የተቀመጠ ሲሆን ይህንን በሰንጠረዥ 5 መሰረት ለገቢ ግብር መስሪያ ቤቱ የሚያሳውቁት እንደሚከተለው ይሆናል።

- የተጣራ ትርፍ ብር 6,500.00 የሚያርፈው ከ 0 — 7200.00 ሲሆን የግብር ምጣኔው 0 በመቶ በመሆኑ ምንም አይከፍልም።

ምሳሌ 2፡- አብነት፣ህይወትና ጓደኞቻቸው የህ/ሽ/ማህበር በሂሳብ መግለጫቸው ላይ እንደተመላከተው ብር 16,500.00 የተጣራ ትርፍ መኖሩ ተረጋግጧል። በዚህም መሰረት ይህ ኢንተርፕራይዝ እንደግለሰብ ማሳወቅ ስለሚገባው በሰንጠረዡ መሰረት ከ7201.00 — 19,800.00 በሚለው ውስጥ የሚወድቅ ስለሆነ የግብር ምጣኔ 10 በመቶ እንዲሁም በዚሁ ምጣኔ ተቀናሽ የሚደረገው ብር 720.00 በመሆኑ ሂሳቡ ሲሰላ የሚመለከተውን ይሆናል፡-

- 16,500.00*10%-720.00 = 930.00 የሚመጣ ሲሆን ኢንተርፕራይዙ ለገቢ መስሪያ ቤቱ ብር 930.00 ከትርፉ ላይ ተቀናሽ አድርጎ ማሳወቅ ይጠበቅበታል።

## 5.3.2 የቅድመ ንግድ ትርፍ ግብር ክፍያ (withholding tax)

በሀገር ዉስጥ ከሚፈጸሙ ክፍያዎች ግብርን ቀንሶ የማስገባት ስልጣን ከጥቃቅን አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በስተቀር ድርጅት፣ የመንግስት መስሪያ ቤት፣ ለትርፍ ያልተቋቋሙ ድርጅቶች ወይም መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች እና በመመሪያ ቁጥር-145/2011 መሰረት ስልጣን የተሰጣቸው የደረጃ- ሀ ግለሰብ ነጋዴዎች ለሚከተሉት ግብይቶች ከሚፈጽሙት ጠቅላላ ክፍያ በአንድ ዕቃ ግዥ ውል 10,000.00 ብር በላይ እና አግልግሎት ክፍያ የአንድ አገልግሎት ግዥ ውል ከ 3,000.00 ብር በላይ በሚፈጽሙ ግዜ 2% እንዲያስገቡ፣ አቅራቢው የታክስ መለያ ቁጥር ታክስ ቀንሰው ለሚያስገቡ ካልሰጠ 30% ቀንሰው የማስገባት ግዴታ አለባቸው።

**ማስታወሻ**

የጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በቅድመ - ግብር ክፍያ ስርዓት መመሪያ ቁጥር 2/2011 አንቀጽ 11 መሰረት የቅድመ -ግብር /Witholding Agent/ አይደሉም።

ምሳሌ የንግድ ሥራ ገቢ ታክስ (ግለሰብ ነጋዴ ከሆነ)

አንድ ግለሰብ ነጋዴ በዓመት ብር 60,000 ግብር የሚከፈልበት ትርፍ በሂሳብ መዝገቡ ይታያል፣ በዓመቱ ውስጥ 2000.00 ብር ቅድመ ግብር ከፍለዋል፣ የዓመቱ የንግድ ስራ ገቢ ግብሩ እንደሚከተለው ይሰላል፡

60,000 በሰንጠረዡ ተራ ቁጥር 4 ውስጥ ይገኛል:: በዚህ መሰረት የሚከፈለዉ የታክስ ስሌት (60,000*.2) - 3630.00-2000 = 6,370.00 ብር ይሆናል::

## 5.3.3 ተቀናሽ የሚደረጉ ወጪዎች

በግብር ዓመቱ የግብር ከፋዩን ግብር የሚከፈልበት ገቢ ለመወሰን በተቀናሽ የሚያዙት ወጪዎች የሚከተሉትን ይጨምራል፡-

በንግድ ስራ ገቢ ውስጥ የተካተቱትን ገቢዎችን ለማግኘት፤ለንግድ ስራ ዋስትና ለመስጠትና የንግድ ስራውን ለማስቀጠል በግብር ከፋዩ በግብር ዓመቱ ውስጥ የተደረጉ አስፈላጊ የሆኑ ወጪዎች፣

- በሂሳብ መግለጫ ሪፖርት አቀራረብ ደረጃዎች በተመለከተው መሰረት የተሰላ በግብር ዓመቱ በግብር ከፋዩ ለተሸጠ የንግድ ዕቃ የወጣ ወጪ፣
- የንግድ ስራ ገቢን ለማግኘት ስራ ላይ የዋሉ ዋጋቸው የሚቀንስ ሀብቶች እና ግዙፋዊ ህልዎት ለሌላቸው የንግድ ስራ ሀብቶች በግብር ዓመቱ የሚታሰበው ጠቅላላ የእርጅና ቅናሽ፣
- ግብር ከፋዩ የንግድ ዕቃን ሳይጨምር በግብር ዓመቱ የንግድ ስራ ሀብትን ሲያስተላልፍ የሚገጥመው ኪሳራ፣
- ለግብር ዓመቱ በዚህ አዋጅ መሰረት ለግብር ከፋዩ በተቀናሽነት የሚፈቅድ ሌላ ማናቸውም ወጪ፣

**ማስታወሻ**

ስለተቀናሽ ወጭዎች አፈጻፀም በወጣ መመሪያ ቁጥር 5/2011 አንጽ 4 ንኡስ አንቀጽ -10 ጥቃቅንና አነስተኛ ኢንተርፕራይዞች በስራ ላይ ላሰማራው አባሉ የሚከፈል ደመወዝ በወጭነት ይያዛል::

## 5.3.4 ተቀናሽ የማይደረጉ ወጪዎች :

- የኩባንያ አክሲዮን ወይም የሽርክና ማህበር መሰረት የሆነውን ካፒታል ለማሳደግ የሚወጣ ወጪ፣
- ከተቀጣሪው የወር ደመወዝ 15 በመቶ በላይ በፈቃደኝነት የሚደረግ የጡረታ ወይም የፕሮቪደንት ፈንድ መዋጮ ፣
- የአክሲዮን ድርሻ እና የትርፍ ድርሻ ክፍፍል፣

- በመድን፣በካሳ ወይም በዋስትና ውል መሰረት የተመለሰ ወይም ሊመለስ የሚችል ወጪ ወይም ኪሳራ፣
- ማንኛውም ሕግ ወይም ውል በመጣስ የሚጣል የገንዘብ ቅጣት ወይም የሚከፈል ካሳ፣
- ግብር ከፋዩ በሂሳብ መዝገቡ የሚይዘው በወቅቱ ወጪ ያልተደረገ ነገር ግን ለወደፊቱ በግብር ዓመቱ ለሚከሰቱ ወጪዎች ወይም ኪሳራዎች መጠባበቂያ ይሆን ዘንድ የሚያዝ ገንዘብ ወይም የመጠባበቂያ ሂሳብ፣
- በዚህ አዋጅ ወይም በውጭ ሀገር የታክስ ሕግ መሰረት የተከፈለ የገቢ ግብር ወይም ተመላሽ የሚደረግ የተጨማሪ እሴት ታክስ፣
- መስሪያ ቤቱን ወክሎ በተለያዩ ቦታዎች ለሚገኝ ተቀጣሪው ከተቀጣሪው ከመቀጠር የሚገኝ ገቢ 10 በመቶ በላይ የሚከፈል የኃላፊነት አበል፣

ከሚከተሉት በስተቀር ለመዝናኛ የሚወጣ ወጪ፣

1. የግብር ከፋዩ የንግድ ስራ የመዝናኛ አገልግሎት መስጠት ሲሆን፣ ወይም
2. ሚኒስትሩ በመመሪያ ተቀናሽ እንዲደረግ በሚፈቅደው ልክ በማዕድን ማውጣት፣በማኑፋክቸሪንግ ወይም በግብርና ስራ የተሰማራ ቀጣሪ ሰራተኞችን ለማዝናናት የሚያወጣው ወጪ (ደንብ 407/2009 እና መመሪያ 5/2011 ይመለከቱ)፣
3. ግብር ከፋዩ አንድን የንግድ ስራ ሀብት ግንኙነት ላለው ሰው ሲያስተላልፍ የሚደርስ ኪሳራ፣
4. የሚኒስትሮች ም/ቤት በሚያወጣው ደንብ ተቀናሽ የማይደረጉ ናቸው የተባሉ ወጪዎች (ደንብ 407/2009 እና መመሪያ 5/2011 ይመለከቱ)

## 5.3.5 ተጨማሪ እሴት ታክስ እና ተርን ኦቨር ታክስ (VAT and ToT)

ተጨማሪ እሴት ታክስና ተርን ኦቨር ታክስ ቀጥተኛ ካልሆኑ ታክሶች በመሆናቸው ምክንያት ለዚህ ማንዋል በማሳያነት ተወስዷል፤ ሌሎች ታክሶችን የሚመለከታቸዉን ታክስ አዋጆችን ይመልከቱ (ኤክሳይዝ ታክስ አዋጅ ቁጥር 1186/2012፣የቴምበር ቀረጥ አዋጅ ቁጥር 110/1998 ይመልከቱ) ::

የተጨማሪ እሴት ታክስ በአዋጅ 285/1994 እና ደንብ ቁጥር 79/1995 ተርን ኦቨር ታክስ አዋጅ ቁጥር 308/1995፣ ማሻሺያ አዋጅ ቁጥር 611/2011 ና የተጨማሪ እሴት ታክስ የግዴታ ምዝገባ የግብይት መጠን ማሻሻያ ሰርኩላር በመንተራስ ይህ ማሳያ ማኑዋል ተዘጋጅተዋል ::

ተጨማሪ እሴት ታክስ በፍጆታ ላይ ወይም በተጠቃሚው ወጪ ላይ የተመሠረተ ታክስ ነው::

ታክስ የሚሰበሰበው ወይም የሚቆረጠው ምርት ከውጭ አገር ወደ አገር ውስጥ ሲገባ /ኢምፖርት ሲደረግ/ ወይም የዕቃና የአገልግሎት ግብይት ሲካሄድ ነው::

የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) መሠረቱ ሰፊ የሆነ በፍጆታ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ላይ የሚጣል ታክስ ነው:: ታክሱ ከአስመጪዎችና ጥሬ ዕቃ አምራቾች አንስቶ እስከ ችርቻሮዎች ድረስ በሚደረጉ የማምረትና የማከፋፈል /የማሠራጨት/ ሂደቶች በሁሉም ደረጃዎች፣

በሚፈጠረው ተጨማሪ እሴት ላይ ይሰበሰባል፡፡

የስሌቱ ቀመርም፡- ከምርት ሽያጭ የተሰበሰበ የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲቀነስ በግብዓት ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ይሆናል (ተከፋይ ተጨማሪ እሴት ታክስ)

በግብዓት ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ማለት ለማምረቻ መሣሪያዎች፣ ለማ ከፋፈልና ለአስተዳደራዊ ተግባራት የተከፈለ ታክስ ያጠቃልላል፡፡

ተጨማሪ እሴት የሚባለው ደግሞ አንድ አምራች ምርቱን ለማምረት ጥሬ ዕቃዎች ገዝቶ በመጨረሻ ምርትነት ለሽያጭ እስከሚያቀርብበት ጊዜ ባለው የምርት ሂደት የሚፈጠር እሴት ነው፡፡ ታክሱ በምርትና ስርጭት ሂደት በሚፈጠር ተጨማሪ እሴት ላይ ብቻ የሚጣል በመሆኑ በታክስ ላይ ታክስ /Tax-on-Tax/ እንዲከፈል አያደርግም፡፡

ይህ ታክስ በግብዓት ማለትም አንድን ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት በሚፈፀም ግዥ የሚከፈል፤በምርት ውጤት ማለትም ምርት በሚሸጥበት ግዜ በመሸጫ ዋጋው ላይ ታክስ የሚከፍል ስለሆነ ተመላሽ ወይም ክሬዲት የማድረግ ሥርዓትን ይከተላል፡፡

### 5.3.5.1 ተጨማሪ እሴት ታክስ ምጣኔዎች

ተጨማሪ እሴት ታክስ ሁለት መጣኔዎች አሉት፡

ሀ. መደበኛ መጣኔ (15%): የታክስ ምጣኔው በመደበኛነት በግብዓት እና በምርት ውጤት ላይ የሚሰላ ምጣኔ ነው፡፡

- የግብዓት ታክስ (Input tax) ማለት ፡- አንድን ምርት ለማምረት ወይም አገልግሎት ለመስጠት በሚፈፀም ግዥ ላይ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ሲሆን፣ የምርት ውጤት ታክስ (Out Put tax) ደግሞ ምርት በሚሸጥበት ግዜ በመሸጫ ዋጋው ላይ ታስቦ የሚከፈል የተጨማሪ እሴት ታክስ ነው፡፡ ታክሱን ማስከፈል የሚችለው ሰው ራሱ የተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ ሆኖ የተመዘገበ ብቻ ነው፡፡

ለ. ዜሮ ምጣኔ (Zero Rating)፡- አቅርቦቱ ዜሮ ከመቶ (0%) የሚከፈልበት ሆኖ ነገር ግን ለአቅርቦቱ በግዥ ወቅት የተከፈለ የተጨማሪ እሴት ታክስ ተመላሽ /ማካካሻ/ ሊጠየቅበት ይችላል፡፡

በአዋጁ መሰረት ዜሮ ተመን የሚባሉት፤

- ወደ ውጪ የሚላኩ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች በመመርያ በሚወስነው መሰረት፣
- ዓለም አቀፍ የሰዎች ወይም የዕቃዎች ማጓጓዣ ተግባር ወይም ከዚህ ጋር በቀጥታ የተገናኙ አገልግሎቶችን እንዲሁም በዓለም አቀፍ በረራ ወቅት ለፍጆታ የሚውሉ የቅባት ዘይቶች እና ሌሎች አላቂ የቴክኒክ ዕቃዎች፣
- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ፣ የመሳሰሉት ናቸው፡፡
- ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የሆኑ ግብይቶች፡- አቅርቦቶችን ከተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ ነፃ ማድረግ ነው፡፡ ከታክስ ነፃ በተደረጉ ግብይቶች ላይ የተጨማሪ እሴት ታክስ

አይከፈልባቸውም:: እንዲሁም ምርቱን ለማምረት ወይም አገልግሎቱን ለመስጠት በተከናወኑ ግዥዎች /ግብዓቶች/ ላይ ግብይቱን ለመፍጠር በግዥዎች /ግብዓቶች/ ላይ የተከፈለ ተጨማሪ እሴት ታክስ ማካካሻ /ተመላሽ/ ሊጠየቅበት አይቻልም:: ከታክስ ነፃ አቅርቦቶች ተ.እ.ታ የማይከፈልባቸው ከመሆናቸውም ሌላ የተጨማሪ እሴት ታክስ የሚከፈልበት ሽያጭ አካል አይደሉም:: በመሆኑም ከታክስ ነፃ አቅርቦቶች ብቻ የሚያቀርብ ሰው ለተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያ አይመዘገብም::

### 5.3.5.2 ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የተደረጉ ግብይቶች

ከታክሱ ነፃ የሆኑ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ምንም አይነት የተጨማሪ እሴት ታክስ /መደበኛም ሆነ በዜሮ ምጣኔ/ የማይከፈልባቸው አቅርቦቶች ማለት ነው:: አንድ ሰው ሙሉ በሙሉ ከታክስ ነፃ በሆኑ ግብይቶች ስራ ላይ የተሰማራ ከሆነ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይነት አይመዘገብም:: ከዚህም በላይ አንድ ሰው/ግብር ከፋይ ቅይጥ አቅርቦት የሚያከናውን ቢሆን ማለትም ታክስ በሚከፈልበትና ከታክስ ነፃ አቅርቦቶች ላይ የተሰማራ ከሆነ ከታክስ ነፃ ለሆኑት አቅርቦቶች የግብዓት ታክስ ማካካሻ ተመላሽ መጠየቅ አይችልም::

በዚህም መሰረት ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የተደረጉ ግብይቶች የሚከተሉት ናቸው::

- ያገለገለ መኖርያ ቤት ሽያጭ እና የመኖርያ ቤት ኪራይ፣
- የፋይናንስ አገልግሎቶች፣
- ለሳንቲሞችና ለሜዳሊያዎች ጥናት አገልግሎት ከሚውሉት በስተቀር የአገር ውስጥና የውጭ አገር ገንዘቦች እና የዋስትና ሰነዶችን ማሰራጨት ወይም ወደ አገር ማስገባት፣
- ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ የሚቀርብ ወርቅ ወደ አገር ማስገባት
- የኤሌክትሪክ፣የኬሮሲንና የውሃ አገልግሎቶች፣
- በሕግ ወይም ስምምነት ከጉምሩክ ቀረጥ እና ከሌሎች ታክሶች ነፃ የተደረጉ ድርጅቶች፣ተቋሞችና ፕሮጀክቶች ወደ አገር የሚያስገቧቸው እቅዎች፣
- ከልዩ ልዩ የአገልግሎት ወይም የኮሚሽን ክፍያዎች በስተቀር የፖስታ አገልግሎት ድርጅት በማቋቋሚያ አዋጁ በተሰጠው ስልጣን መሰረት የሚያቀርባቸው እቃዎችና አገልሎቶች፣
- የትራንስፖርት አገልሎት፣
- ከ60% በላይ ሰራተኞቹ የአካል ጉዳተኞች የሆኑበት አካል ጉዳተኞችን የሚያሰራ ድርጅት የሚያቀርባቸው እቃዎችና አገልግሎቶች፣
- መጽሐፍት እና የታተሙ ጽሁፎች፣
- ዳቦ፣እንጀራ እና ወተት፣
- ለግብርና ግብዓት በቀጥታ የሚውሉ እንደ ማዳበሪያ፣ፀረ ተባይ ኬሚካሎችና ምርጥ ዘር በአገር ውስጥ ሲሸጡና ከውጭ አገር ሲገቡ፣ እና ሌሎችም የተካተቱበት ቢሆንም ለኢንተርፕራይዞች በቂ ነው በሚል የቀረበ ቢሆንም የበለጠ ለማወቅ በደንብ ቁጥር 79/1994 ክፍል ሁለት አንቀፅ 8 ማየት ይቻላል::

### 5.3.5.3 ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች

ከታክሱ ነፃ ያልተደረጉ ማናቸውም በኢትዮጵያ ውስጥ የተሰሩ እቃዎች ወይም የተሰጡ አገልግሎቶች ታክስ የሚከፈልባቸው ግብይቶች ናቸው፡፡ አንድ ሰው እነዚህ እቃዎችን ወይም አገልግሎቶችን ከንግድ ስራው ላይ በስጦታ መልክ ለሌላ ሰው ቢያበረክት በወቅቱ ባለው የእቃዎቹ ወይም የአገልግሎቱ የገበያ ዋጋ ላይ በመመስረት የተጨማሪ እሴት ታክሱን ማሰብ ይኖርበታል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር የዕቃ ልውውጥ ቢያካሂድ ለልልውጥ ባቀረበው እቃ ሙሉ ዋጋ ላይ የተጨማሪ እሴት ታክሱን በማሰብ የምርት ውጤት ተጨማሪ እሴት ታክስ ከፋይ ይሆናል፡፡

### 5.3.5.4 የተጨማሪ እሴት ታክስን መመዝገብ

የተጨማሪ እሴት ታክስን ምዝገባ በተመለከተ በሶስት ዓይነት ይታያሉ፡፡

1. የግዴታ ምዝገባ

ማናቸውም ሰው የ12 ወራት ጊዜ ውስጥ ያከናወነው ታክስ የሚከፈልበት ግብይት ከብር 1,000,000.00 የሚበልጥ ወይም እንደሚበልጥ የሚታሰብ ከሆነ የድርጅቱ /የኢንተርፕራይዙ ስራ የሚያካሂደው ሰው ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ የግብር ማህደሩ በሚገኝበት ክ/ከተማ/ወረዳ/ ዞን ገቢዎች ቅ/ፅ/ቤት በመገኘት መመዝገብ አለበት፡፡

2. የፈቃደኝነት ምዝገባ

በማናቸውም ተከታታይ 12 ወራት የንግድ ስራ እንቅስቃሴ ውስጥ ታክስ የሚከፈልበት ሽያጭ ከብር 1,000,000.00 በታች ሆኖ ቢያንስ 75% የዘውትር ዕቃ አቅርቦቱ ወይም አገልግሎት የመስጠት ስራው ለተጨማሪ ዕሴት ታክስ ለተመዘገቡ ሰዎች ከሆነ በፍቃደኝነት ምዝገባ ለመመዝገብ ማመልከት ይቻላል፡፡

3. የዘርፍ ምዝገባ

በተ.ቁ 1 እና 2 ከተገለፀው አግባብ በተጨማሪ የሽያጭ ገቢ የገደባቸውና በንግድ ባህሪያቸው በታክሱ ስርዓት መታቀፍ ለታክሱ ወጥ አፈፃፀም በማሰብ እንዲሁም በተመዘገቡና ባልተመዘገቡ ግብር ከፋዮች መካከል ፍትሐዊ የገበያ ውድድር እንዲኖር ለማስቻል የሚከተሉት የንግድ መስክ እንቅስቃሴዎች በዘርፍ ተለይተው እንዲመዘገቡ ተደርጓል፡፡

በዚህም መሰረት፡- ወርቅ ቤቶች፣ ኤሌክትሮኒክስ (ፍሪጅ፣ዴክ፣ቲቪ፣ዲቪዲ፣ቪሲዲ ወዘተ--) ዱቄት ፋብሪካዎች፣ አስመጪዎች፣ ጫማ ፋብሪካዎች፣ ከደረጃ 10 (ከ1-9) በላይ የሚገኙ ስራ ተቋራጮች፣ ኮምፒውተርና የኮምፒውተር መለዋወጫ፣ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች (በተለይ የቆዳ አምራች፣ ከቆዳ የሚሰሩ አልባሳት ወይም ቦርሳዎችን የሚያመርቱ ወይም የሚሸጡ) እና የፕላስቲክና የፕላስቲክ ውጤቶች ላይ የተሰማሩ ኢንተርፕራይዞች/ድርጅቶች በዘርፋቸው መሰረት እንዲመዘገቡ ይሆናል፡፡

## የተጨማሪ እሴት ታክስ ስሌት ምሳሌዎች

ምሳሌ :- አቤኔዘር እና ጓደኞቹ የተባለ የማምረቻ ህ/ሽ/ማህበር(ኢንተርፕራይዝ) ጥሬ ዕቃ ገዛ

በግዥ ደረጃ ላይ

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ጥሬ ዕቃ የተገዛበት ዋጋ | 2000.00 |
| 2. | የተጨማሪ እሴት (15% መጣኔ ) | 300.00 |
| 3. | የዕቃው ዋጋ ተ.እ.ታ (1+2) | 2300.00 |
| 4. | የዕቃው ዋጋ ወደ ማምረቻ ክፍል ሲተላለፍ የሚኖር ዋጋ | 2000.00 |

ሲመረትና ለጅምላ ሻጭ ሲተላለፍ፡

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ጥሬ ዕቃ | 2000.00 |
| 2. | ጉልበትና ሌሎች የፋብሪካ ወጪዎች | 2000.00 |
| 3. | በፋብሪካ ተመረተው ያለቀለት ዕቃ | 4000.00 |
| 4. | የትርፍ መጠን (ህዳግ)15% | 600.00 |
| 5. | የአምራቹ የምርት መሸጫ ዋጋ | 4600.00 |
| 6. | ተ.እ.ታ (4600*15 % | 690.00 |
| 7. | የዕቃው ዋጋ በጅምላ መሸጫ ቦታ ተ.እ.ታ ተጨምሮ | 5290.00 |

**ማስታወሻ**

- ከላይ በተጠቀሰው ምሳሌ የተገዛው ጥሬ ዕቃ በሙሉ ወደ ፋብሪካ ገብቶ ከፋብሪካም ምርት ሆኖ የወጣ ነው::
- የድርጅቱ የትርፍ መቶኛ ከምርቱ ማምረቻ ዋጋ ላይ 15% ነው::

አምራቹ ለገቢ መ/ቤት ማሳወቅና መክፍል ያለብት ተ.እ.ታ ፡

በሽያጭ ላይ የሚከፈል ታክስ ሲቀነስ ከግዥ ላይ በደረሰኝ የተከፈለ ታክስ (690-300)= 390.00 ነው::

ቸርቻሪ ነጋዴ

| | | |
|---|---|---|
| 1. | ከጅምላ ነጋዴው የገዛበት ዋጋ | 4600.00 |
| 2. | የትርፍ መጠን (ህዳግ) ሌሎች ወጪዎችን ጨምሮ | 750.00 |

3. የዕቃው ዋጋ በችርቻሮ ንግድ ላይ (1+2) 5350.00
4. የተጨማሪ እሴት ታክስ ምጣኔ 15% 802.50

ለሸማቹ የመሸጫ ዋጋ (3+4) 6152.50

**ማስታወሻ**

ቸርቻሪው ኢንተርፕራይዝ/ነጋዴ ለገቢ መ/ቤት ማሳወቅና መክፍል ያለብት ተ.እ.ታ ፣በሽያጭ ላይ የሚከፈል ታክስ ሲቀነስ ከግዥ ላይ በደረሰኝ የተከፈለ ታክስ (802.5-690) =112.50

ነጋዴው የተ.እ.ታ ከሆነ ተመዝጋቢ ካልሆነ ደግሞ የሽያጩን (5350) 2% ተርን ኦቨር ታክስ 107.00 ብር በማሳወቅ ይከፍላል።

### 5.3.5.5 ታክስ በሚከፈልበት ግብይት ዋጋ ላይ ተቀናሽ ተደረጎ ስለሚያዝ ታክስ

በመመሪያ ቁጥር 27/2002 በተሠጠው የውክልና ሥልጣን መሰረት የፌደራል፣የክልል፣እና የከተማ የመንግስት መስሪያ ቤቶች፤ የመንግስት የልማት ድርጅቶችና የተመረጡ የግል ድርጅቶች በሚያከናውኑት ተ.እ.ታ የሚከፈለበት ግብይት ላይ ለአቅራቢው (ለሻጭ) መከፈል ካለበት የተጨማሪ እሴት ታክስ 50% ቀንሶ በማስቀረት ወር በገባ በ30 ቀናት ለሚመለከተው ገቢ መስሪያ ቤት ያስገባል፣ቀሪውን 50% ደግሞ ለአቅራቢው ከዕቃው ወይም አገልግሎት ክፍያ ጋር ወዲያው ይከፍላል፤ የእቃ /አገልግሎት ክፍያ ቅድሚያ ወይም ግማሽ ክፍያ ከሆነ ታክሱ በዚሁ ክፍያ ላይ በሚታሰብ ታክስ 50% ተቀናሽ እንደሚደረግ በመመሪያ ቁጥር 60/2012 ተደንግጓል፣ ለተጨማሪ ማብራሪያ ሁለቱን መመርያዎች ይጠቀሙ።

### 5.3.5.6. ተርን ኦቨር ታክስ

በአገር ውስጥ በሚከናወን የዕቃ ወይም የአገልግሎት ሽያጭ ወቅት በየደረጃው ማለትም የተጨማሪ እሴት ታክስ በማይሰበሰብባቸው እቃዎች ወይም አገልግሎቶች ላይ የሚጣል የተጨማሪ እሴት ታክስ ማካካሻ ነው። በሌላ አነጋገር በግብር ከፋዩ ሕብረተሰብ በታክስ አከፋፈል ላይ ፍትሐዊነትን ለማስፈን እና ሁሉም የኢኮኖሚ ዘርፍ በአገር ዕድገት የራሱን አስተዋፅኦ ያበረክት ዘንድ ለተጨማሪ እሴት ታክስ ያልተመዘገቡ /የመመዝገብ ግዴታ ያልተጣለባቸው/ ግብር ከፋዮች በተርን ኦቨር ታክስ ስርዓት እንዲታቀፉ ሲባል የተርን ኦቨር ታክስ ስራ ላይ ውሏል።

ታክሱ የሚሰላበት ዋጋ የዕቃው ወይም የአገልግሎቱ ጠቅላላ የሽያጭ ዋጋ ነው።

የታክሱ ምጣኔ፡-

1. በማናቸውም በአገር ውስጥ በሚሸጡ ዕቃዎች ላይ 2% (ሁለት በመቶ)፣
2. በአገር ውስጥ በሚሰጡ አገልግሎቶች ላይ፤

ሀ. የስራ ተቋራጭ፣የእህል ወፍጮ ቤቶች፣የትርራክተሮችና የኮምባይነር ሀርቨስተሮች አገልግሎቶች 2% (ሁለት በመቶ) ፣

ለ. ሌሎች አገልግሎቶች 10 %( አስር በመቶ) ተርን ኦቨር ታክስ ይከፍላሉ።

5.3.5.7 ከተርን ኦቨር ታክስ ነፃ የተደረጉ ግብይቶች

ከተጨማሪ እሴት ታክስ ነፃ የተደረጉ ግብይቶች ከተርን ኦቨር ታክስም ነፃ ተደርገዋል።

## የተርን ኦቨር ታክስ ስሌት

ምሳሌ፡- በልብስ ስፌት ላይ የተሰማራ ኢንተርፕራይዝ በየ3 ወሩ ማሳወቅ የሚጠበቅበት ሲሆን፤በዚህ መሰረት ኢንተርፕራይዙ በጥር ወር ስራ ጀምሮ በ3 ወራት ውስጥ ባሳተመው የተርን ኦቨር ታክስ የሽያጭ ደረሰኝ ድምር ብር 4200.00 ሰብስቧል።

ስለሆነም በሚያዝያ ወር የሚከፍለው ብር 4200*10%= 420.00 ይሆናል ማለት ነው፡

5.3.5.8 ሌሎች ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች፣

ሌሎች ያልተብራሩ ቀጥተኛ ያልሆኑ ታክሶች፣ ኤክሳይዝ ታክስ፣ቴምበር ቀረጥ ፣የጉምሩክ ቀረጥ እና ሱርታክስን አብዛኛውን ጥቃቅን ኢንተርፕራይዞችን ስለማይመለከታቸው በቅደም ተከተል አዋጅ ቁጥር 1186/2012፣110/1990፣859/2007እና መቁጥ133/1998) በመመልከት እንደ አስፈላጊነታቸው መጠቀም ይቻላል።

ኤክሳይዝ ታክስ፤ኤክሳይዝ ታክስ የቅንጦት እንዲሁም መሰረታዊ በመሆናቸው ምክንያት የገበያ ፍላጎታቸው በማይቀንስ ዕቃዎች እና የህብረተሰቡን ጤና በሚጎዱና የማህበራዊ ችግር በሚያስከትሉ ዕቃዎች ላይ አጠቃቀሙን ለመቀነስ ሲባል በተወሰኑ ዕቃዎች ወይም አገልግሎቶች ላይ የሚጣል የታክስ አይነት ነው፤ስሌቱም ወደ አገር በሚገቡ እቃዎች ላይ እቃዎቹ ወደ አገር ሲገቡ ቀረጥ ሳይጨምርላቸዉ ዋጋ (C.I.F) እና የጉሙሩክ ቀረጥ ተደምረው የአዋጁ ሠንጠረዥ 1 ውስጥ በሚመለከተው ምጣኔ ሲባዛ የሚገኘው ውጤት ሆኖ እቃዎቹ ከጉሙሩክ ጣቢያ ሲወጡ ታክሱ የሚከፈል ይሆናል፤ በሀገር ውስጥ በሚመረቱ ምርቶች ላይ ደግሞ የፋብሪካ መሸጫ ዋጋ ላይ የአዋጁ ሠንጠረዥ 1 ውስጥ በሚመለከተውን ምጣኔ በማባዛት የሚገኝ ውጤት ሆኖ ምርቱ ከፋብሪካ ሲወጣ ታክሱን የመክፈል ግዴታ የሚኖር ይሆናል።

## ቴምበር ቀረጥ

በተወሰኑ የሰነድ አይነቶች ላይ የሰነዶቹን ህጋዊነት ለማረጋገጥና ለመንግሰት ገቢ ለማስገኘት የተደነገገ ሲሆን አከፋፈሉ በአዋጁ ሠንጠረዥ ውስጥ የተመለከተውን ምጣኔ በሰነዱ ዓይነት ወይም በሰነዱ ዋጋ በማባዛት ይሆናል፡፡

ቀረጥ የመክፈል ግዴታ በሰነዱ ተጠቃሚ የሚሆነው ሰው ላይ የተጣለ ነው፡፡ በሌሎች ሁኔታዎች ለምሳሌ ሰነዱን የሚሰራ ወይም የሚሰጥ ሰው፣ ኪራይ ሲሆን ተከራይ፣ የሥራ ውል ሲሆን አሰሪ፣ የመያዣ ውል ሲሆን ተበዳሪ፣ የንብረት ባለቤትነት ሲሆን ባለቤትነቱ የሚመዘግብለት ሰው፣ በግልግል የሚወሰኑ በጋራ፣ የህብረት ስምምነት አሰሪና ሰራተኛ በጋራ የመክፈል ግዴታ አለባቸው፡፡

የቴምብር ቀረጥ ያለመክፈል በወንጀል ማስጠየቁ እንደተጠበቀ ሆኖ ሰነዱ በውል ወይም በህግ ማስረጃ የመቀበል ስልጣን ባለው ሰው ወይም የመንግስት መ/ቤት ዘንድ በማስረጃነት ተቀባይነት አይኖረውም፡፡ ሆኖም ሊከፈልባቸው የሚገባውን በሁለት እጥፍ ከከፈሉ በማስረጃነት ተቀባይነት ሊያገኙ ይችላሉ፡፡

## የጉምሩክ ቀረጥ

ኮንትሮባንድና ሌሎች የንግድ ማጭበርበር ወንጀሎችን ለመከላከል እንዲሁም የሀገሪቱን የኢኮኖሚ እድገት ለመደገፍና ከሌሎች ሀገራት ጋር ያለውን የንግድ ግኑኙነት/ስምምነቶችን ለማሻሻል ሲባል ወደ ሀገር በሚገቡ ዕቃዎች ዋጋ (C.I.F) ላይ በአዋጁ ሰንጠረዥ ላይ በተቀመጠው ምጣኔ በማባዛት ተሰልቶ እቃዎቹ ከጉምሩክ ጣቢያ ሲወጡ የሚከፈል ሲሆን፤ ከሀገር በሚወጡ እቃዎች ላይ ደግሞ የዕቃዎቹ መሸጫ ዋጋ እና ከኢትዮጵያ መውጫ ድረስ የተከፈሉ ወጭ ድምር ላይ በሰንጠረዥ ባለው ምጣኔ ተባዝቶ ይሰላል፡፡

## ሱር ታክስ

በደንብ ውስጥ አንቀፅ 5 ስር ነጻ ከተደረጉ በስተቀር በሁሉም ወደ አገር በሚገቡ እቃዎች ላይ 10 በመቶ እቃዎች ዋጋ (c.i.f+ excise tax+vat) ድምር ላይ እየተጣለ የሚሰበሰብ ነው፡፡

**ለምሳሌ**

ብርሃን ኢንተረፕራይዝ በ2012 ከረሜላ ለማምረት በጥቃቅንና አነስተኛ ተደራጅቶ ስራ ጀምሯል፡፡ በበጀት ዓመቱ በነሀሴ ወር 2012 ዓም 40 ደርዘን ከረሜላ በፋብሪካ መሸጫ ዋጋ በብር 20,000 ለአንድ ህፃናት መርጃ ድርጅት በዱቤ ሸጠ፡፡ ይህን ከረሜላ ለማምረት በ12,000 ብር ስኳር፣ ሌሎች ግብዓትና ስራ ማስኪያጃ ወጪዎች አውጥቷል፡፡ በዚሁ መሰረት ኢንተርፕራይዙ ሊከፍል የሚገባቸውን ታክስ ዓይነት እና መጠን እንደሚከተለው ይሆናል፡፡

መልስ

1. ኢንተርፕራይዙ ሲመሰረት የመመስረቻ ጽሁፍና ውል በኬዝ በብር 350.00
2. ኤክሳይዝ ታክስ ተከፋይ = 20,000*30% = 6000
3. ተእታ=ግብአት ታክስ =12,000/1.15*15% = 1565.21

   ውጤት ታክስ= (20,000+6,000) *15% = 3900

   ተእታ ተከፋይ= (2-1) = 3,900-1565.21 = 2334.79

4. ቅድመ ግብር ታክስ = 20,000*2% = 800

# ምሳሌዎች

## ምሳሌ 1 በአገልግሎት ዘርፍ

### በጥቃቅንና አነስተኛ በአገልግሎት ዘርፍ በኮምፒውተር ጥገና ላይ የተሰራ የሂሳብ አያያዝ ማሳያ

የናት የኮምፒውተር ጥገና የህ/ሽ/ማህበር ከመስከረም/2010 ጀምሮ በአገልግሎት ዘርፍ ለመስራት ብር 50,000.00 እኩል በማዋጣት በብር 150,000.00 መነሻ ካፒታል በጋራ ስራ ጀመሩ:: ኢንተርፕራይዙ የበጀት ዓመት ከሐምሌ 1/2009 እስከ ሰ ኔ 30/2010 ዓ.ም ድረስ ሲሆን በዚህ መሰረት የሚከተሉትን እንቅስቃሴዎችን አካሂዷል::

ክስተት 1 የንግድ ባለቤቶቹ መጀመርያ ለሚሰሩት ስራ መዋለ ነዋይ ሲያፈስሱ

የናት የሕ/ሽ/ማህበር መስከረም 2/2010 ዓ.ም በሶስት ጓደኛሞች ከግላቸው በብር 50,000.00 እኩል መጠን በማዋጣት በአገልግሎት ዘርፍ ተቋቋሙ::

ክስተት 2 የቢሮ መገልገያ ግዥ (በገንዘብ)

የናት የሕ/ሽ/ማህበር ለቢሮ ስራ አገልግሎት የሚውል ኮምፒውተር በቀን 10/1/10 ዓ.ም በብር 7000.00 ሻት ተመዝጋቢ ከሆነ ድርጅት በደረሰኝ ቁጥር 1001 በገንዘብ ተገዛ::

ክስተት 3 የፅ/መሳርያ በዱቤ ግዥ መፈፀም

በቀን 05/02/10 ዓ.ም ኢንተርፕራይዙ የፅ/መሳርያ ግዥ (ወረቀቶችና ሌሎች) ከሻት ተመዝጋቢ ከሆነ ድርጅት በዱቤ ገዛ::

ክስተት 4 የናት ኢንተርፕራይዝ በገንዘብ አገልግሎት ሰጠ

በቀን 11/02/10 ዓ.ም ኢንተርፕራይዙ ብር 7000.00 ከነሻቱ የኮምፒውተር

ፕሮግራም በመስራት በቫት ደረሰኝ ቁጥር 211 ተቀበለ፡፡

ክስተት 5 የማስታወቂያ አገልግሎት በዱቤ አሰራ

የናት ሕ/ሽ/ማህበር በቀን 15/03/10 ዓ.ም ከአገር ውስጥ የማስታወቂያ ድርጅት ብር 2500.00 በዱቤ ማስታወቂያ አሰራ፡፡

ክስተት 6 ኢንተርፕይዙ በገንዘብና በዱቤ አገልግሎት ሰጠ፡፡

ኢንትርፕራይዙ በቀን 20/3/10 ዓ.ም ለደንበኛው አገልግሎት በመስጠት ብር 1500.00 በገንዘብ ሲቀበል የተቀረውን ብር 2500.00 በሁለት ሳምንት ውስጥ ደንበኛው እንደሚከፍለው ነግሮት ተስማማ ፡፡ (ቫት ሳይጨመርበት)

ክስተት 7 ወጪን በተመለከተ፡፡

ኢንተርፕራይዙ ቤት ኪራይ ብር 600.00፤ ለአንድ ሰራተኛ የደሞዝ ክፍያ ብር 900.00 እና ብር 200 ለመብራት ክፍያ አወጣ፡፡ (26/3/10)

ክስተት 8 የነበረ ዕዳን መክፈልን በተመለከተ

በዱቤ ወስዶት የነበረውን የማስታወቂያ አገልግሎት ብር 2500.00 ለድርጅቱ በደረሰኝ ቁጥር 111 ከፈለ ክስተቱን እንደሚከተለው ለማስቃኘት ተሞክሯል፡፡ (5/4/10)

ክስተት 9 በዱቤ ሰጥቶት የነበረውን በገንዘብ ሲቀበል

በክስተት 6 ላይ በዱቤ ለሰጠው አገልግሎት ብር 3100.00 ገንዘብ ተቀብሎ ወደ ኢንተርፕራይዝ ካዝና አስገባ በዚህ መሰረት ክስተቱን እንደሚከተለው ይሆናል፡፡ (12/4/10)

ክስተት 10 የኢንተርፕራይዙ ባለቤቶቹ ትርፍ ክፍፍል አደረጉ፡፡

የናት ኢንተርፕራይዝ ብር 1300.00 ባለቤቶቹ ትርፍ ክፍፍል አደረጉ፡፡

**ጥያቄ**

1. በትራንሳክሽኑ መሰረት የሂሳብ መደብ እና የሂሳብ መለያ ቁጥር አዘጋጅ
2. ትራንሳክሽኖቹን በጥምር ሂሳብ መዝገብ ላይ አስፍር
3. ወደ ሂሳብ ቋት አሳልፍ
4. የሂሳብ መሞከሪያ ሚዛን አዘጋጅ
5. ማስተካከያ ስራ
6. የሂሳብ መግለጫዎችን አዘጋጅ

1.የናት የኮምፒውተር የጥገና አገልግሎት ኢንተርፕራይዝ የሂሳብ መደቦች እና መለያ ቁጥሮች እንደሚከተለው ቀርቧል::

**የናት የኮምፒውተር ጥገና የህ/ሽ/ማህበር**

**የሂሳብ አርዕስትና መለያ ቁጥር**

| የሂሣብ መደቦችና ርዕሶቻቸው | የሂሣብ መለያ ቁጥር | የሂሣብ መደቦችና ርዕሶቻቸው | የሂሣብ መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|
| ሀብት/Assets/<br>ጥሬ ገንዘብ<br>ሂሣብ ተሰብሳቢ<br>ቫት ተመላሽ/ተሰብሳቢ<br>የፅህፈት መሳርያ<br>ቋሚ ዕቃ/ኮምፒዉተር<br>የዕርጅና ቅ/ኮምፒ/<br>2. ዕዳ /Liability/<br>በዱቤ የተወሰደ<br>ቫት ተከፋይ<br>ተከፋይ የገቢ ግብር | 101<br>102<br>103<br>104<br>105<br>106<br><br>201<br>202<br>203 | 3. አንጡራሀብት /Capital/<br>የናት<br>ትርፍ ክፍፍል<br>ሪተይንድ ኢህርኒንግ<br>4. ገቢ /Revenue/<br>ሽያጭ ገቢ<br><br>5. ወጪ /Expenses/<br>የማስታወቂያ ወጪ<br>የቤት ኪራይ ወጭ<br>የደመወዝ ወጪ<br>የኤሌክትሪክ ወጪ<br>የዕ/ቅ/ ኮምፒዉተር ወጪ<br>የጽሕፈት መሣሪያ ወጪ | 301<br>302<br>303<br>400<br>402<br><br>501<br>502<br>503<br>504<br>505<br>506 |

2. የናት የኮምፒውተር ጥገና ህ/ሽ/ማህበር የሂሳብ እንቅስቃሴውን ተከትሎ የተዘጋጀው የጥምር ሂሳብ መዝገብ እንደሚከተለው ይሆናል።

| ቀን | መግለጫ | ማጠቀሻ | ገንዘብ በባንክ | | ተሰብሳቢ | | የፅ/መሳርያ | | ቫት | | ኮምፒውተር | | ዱቤ | | አን. ሀብት | ሽያጭ | የማስታወቂያ ወጪ | የቤት ኪ. ወጪ | የኤሌ. ወጪ | የደሞዝ ወጪ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | DR | CR | DR | CR | DR | CR | DR | CR | DR | CR | DR | CR | CR | CR | DR | DR | DR | DR |
| 2/1/10 | ዕጣ መዋጮ | | 150,000 | | | | | | | | | | | | 150,000 | | | | | |
| 10/1/10 | ኮምፒውተር ግዥ | | | 8,050 | | | | | 1,050 | | 7,000 | | | | | | | | | |
| 5/2/10 | የፅ/መሳርያ ግዥ | | | | | | 1,391.3 | | 208.70 | | | | | 1,600 | | | | | | |
| 11/2/10 | የኮምፒውተር ጥገና አገልግሎት ሰጠ | | 7,000 | | | | | | | 913.05 | | | | | | 6,086.95 | | | | |
| 15/3/10 | በዱቤ ማስታወቂያ አሰራ | | | | | | | | | | | | | 2,500 | | | 2,500 | | | |
| 20/3/10 | የኮምፒውተር ጥገና አገልግሎት ሰጠ | | 1,500 | | 3,100 | | | | | | | | | | | 4,000 | | | | |
| 26/3/10 | የቤትኪራይ፣ደሞዝ፣መብራት፣ክፍያ ተፈፀመ | | | 1,700 | | | | | | | | | | | | | | 600 | 200 | 900 |
| 5/4/10 | ዕዳ ተከፈለ | | | 2,500 | | | | | | | | | 2,500 | | | | | | | |
| 12/4/10 | በዱቤ የተሸጠ ተሰበሰበ | | 3100 | | | 3100 | | | | 600 | | | | | | | | | | |
| 30/10/10 | ድምር | | 161,600 | 12,250 | 3,100 | 3,100 | 1,391.3 | 0 | 1,258.7 | 1,513.05 | 7000 | 0 | 2500 | 2500 | 150,000 | 10,086.95 | 2500 | 600 | 200 | 900 |
| ትክክለኛ ሚዛን | | | 149,350 | | 0 | | 1,391.3 | | -254.35 | | 7000 | | 0 | | 150,000 | 10,086.95 | 2500 | 600 | 200 | 900 |

3. በጥምር መዝገብ የተመዘገበውን ሂሳብ ወደ ሂሳብ ቋት ሲያልፍ የሚከተለው ይሆናል፡፡

የአካውንት ስም ገንዘብ

የአካውንት ቁጥር 101

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2/1/10 | የአባላት መዋጮ | | 150,000.00 | | 150,000.00 |
| 10/1/10 | ኮምፒውተር ግዢ | | | 8,050.00 | 141,950.00 |
| 11/2/10 | ሽያጭ | | 7,000.00 | | 148,950.00 |
| 20/3/10 | | | | | |
| | ሽያጭ | | 1,500.00 | | 150,450.00 |
| 26/3/10 | ወጪዎች | | | 1,700.00 | 148,750.00 |
| 5/4/10 | ዕዳ ተከፈለ | | | 2500.00 | 146,250.00 |
| 12/4/10 | ከዱቤ የተሰበሰበ | | 3,100.00 | | 149,350.00 |

የአካውንት ስም ተሰብሳቢ

የአካውንት ቁጥር 102

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 20/3/10 | ሽያጭ በዱቤ | | 3100.00 | | 3100.00 |
| 12/4/10 | የተሰበሰበ | | | 3100.00 | 0 |
| | | | | | |

የአካውንት ስም ቫት

የአካውንት ቁጥር 103

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 10/1/10 | ኮምፒውተር ግዢ | | 1050.00 | | 1050.00 |
| 5/2/10 | የፅ/መሳርያ ግዢ | | 208.70 | | 1258.70 |
| 11/2/10 | ሽያጭ | | | 913.10 | 345.60 |
| 20/3/10 | ሽያጭ | | | 600.00 | 254.65 |
| | | | | | |

የአካውንት ስም የፅ/መሳርያ

የአካውንት ቁጥር 104

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 5/2/10 | የፅ/መሳርያ ግዢ | | 1391.30 | | 1391.30 |
| 30/10/10 | ማስተካከያ | | | 1000.00 | 391.30 |

የአካውንት ስም ኮምፒውተር

የአካውንት ቁጥር 105

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 10/1/10 | ግዢ | | 7000.00 | | 7000.00 |
| 30/10/10 | ማስተካከያ | | | 700.00 | 6300.00 |

የአካውንት ስም የተ/ዕ/ቅና/ ኮምፒውተር

የአካውንት ቁጥር 106

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 30/10/10 | ማስተካከያ | | | 700.00 | 700.00 |

የአካውንት ስም ዕዳ

የአካውንት ቁጥር 201

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| 5/2/10 | የፅ/መሳርያ ግዢ | | | 1600.00 | 1600.00 | |
| 15/3/10 | ማስታወቂያ በዱቤ ተሰራ | | | 2500.00 | 4100.00 | |
| 5/4/10 | ተከፈለ | | 2500.00 | | 1600.00 | |

የአካውንት ስም አንጡራ ሀብት

የአካውንት ቁጥር 301

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 2/1/10 | መዋጮ | | | 150,000.00 | 150,000.00 |

የአካውንት ስም ትርፍ ክፍፍል

የአካውንት ቁጥር 302

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 30/10/10 | ትርፍ ክፍፍል አደረጉ | | 1300.00 | | 1300.00 |
| 30/10/10 | መዝጊያ | | | 1300.00 | 0 |
| | | | | | |

የአካውንት ስም ሽያጭ

የአካውንት ቁጥር 401

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 11/2/10 | ሽያጭ | | | 6086.95 | 6086.95 |
| 20/3/10 | ሽያጭ | | | 4000.00 | 10,086.95 |
| 30/10/10 | መዝጊያ | | 10086.95 | | 0.00 |

የአካውንት ስም የማስታወቂያ ወጪ

የአካውንት ቁጥር 501

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 15/3/10 | ለማስታወቂያ ስራ በዱቤ | | 2500.00 | | 2500.00 |
| 5/4/10 | መዝጊያ | | | 2500.00 | 0.00 |

የአካውንት ስም የቤት ኪራይ ወጪ

የአካውንት ቁጥር 502

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 26/3/10 | የቤት ኪራይ ተከፈለ | | 600.00 | | 600.00 |
| 30/10/10 | መዝጊያ | | | 600.00 | 0.00 |

የአካውንት ስም የደሞዝ ወጪ

የአካውንት ቁጥር 503

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 26/3/10 | የደሞዝ ተከፈለ | | 900.00 | | 900.00 |
| 30/10/10 | መዝጊያ | | | 900.00 | 0.00 |

የአካውንት ስም የመብራት ወጪ

የአካውንት ቁጥር 504

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 26/3/10 | የመብራት ተከፈለ | | 200.00 | | 200.00 |
| 30/10/10 | መዝጊያ | | | 200.00 | 0 .00 |

የአካውንት ስም የእርጅና ቅናሽ ኮምፒዩተር ወጪ

የአካውንት ቁጥር 505

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 26/3/10 | ማስተካከያ | | 700.00 | | 700.00 |
| 30/10/10 | መዝጊያ | | | 700.00 | 0.00 |

የአካውንት ስም የፅህፈት መሳሪያ ዕላቂ ወጪ

የአካውንት ቁጥር 506

| ቀን | መግለጫ | ማጣቀሻ | ዴቢት | ክሬዲት | ባላንስ |
|---|---|---|---|---|---|
| 26/3/10 | ማስተካከያ | | 1000.00 | | 1000.00 |
| 30/10/10 | መዝጊያ | | | 1000.00 | 0.00 |

4. የኢንተርፕራይዙ የሂሳብ መሞከሪያ ሚዛን

## የናት የሕ/ሽ/ማህበር

ያልተስካከለ የሒሳብ መሞከሪያ ሚዛን

ሰኔ 30/2010 ዓ.ም

ባንክ ገንዘብ -------------------------------------- 149,350.00

የፅ/መሳርያ ------------------------------------------ 1,391.30

ኮምፒውተር ------------------------------------- 7000.00

ብድር ----------------------------------------------------------------------------------- 1600.00

ቫት ተከፋይ ----------------------------------------------------------------------------- 254.35

ካፒታል ---------------------------------------------------------------------------------- 150,000.00

ሽያጭ -----------------------------------------------------------------------------10,086.95

የማስታወቂያ ወጭ ------------------------------2500.00

የቤት ኪራይ ወጭ ------------------------------ 600.00

የኤሌክትሪክ ወጭ ------------------------------- 200.00

የደሞዝ ወጪ ------------------------------------ 900.00

161,941.30 161,941.30

5. የኢንተርፕራይዙ የሂሳብ ማስተካከያ ስራ

## የሂሣብ ማስተካከያ የተደረገላቸውን ሂሳቦች ወደ ቋት ማስተላለፍ

በአብዛኛው ለትርፍ በተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶች በበጀት ዘመኑ የሥራ ሂደት ውስጥ ማስተካከያ የሚያስፈልጋቸው የገቢ ወይም የወጪ ክስተቶች መፈጠር አይቀሬ ነው:: እነዚህም ክስተቶች እንደ አላቂ የጽሕፈት መሳሪያዎች፣ ኢንሹራንስ፣ ተሰብሳቢ ሂሣቦች፣ የእርጅና ወጪ/ቅናሽ/፣ ያልተሸጡ የሽያጭ ዕቃዎች፣ወዘተ ካላቸው ልዩ ባሕሪ ሳይመዘገቡ እስከ ሂሣብ ዘመኑ መጨረሻ ድረስ ይቆያሉ:: በመጨረሻም በዓመቱ ሂሣብ ውስጥ ለማካተት እንዲቻል የሂሣብ ማስተካከያ በወርክሽት ላይ ይሰራላቸውና ቋሚ መዝገብ ላይ በማስፈር ወደ የሚመለከታቸው ቋቶች

እንዲተላለፉ ይደረጋል፡፡

ስለሆነም የናት የሕ/ሽ/ማህበር ቋሚ ዕቃ የገዛው ኮምፒውተር ብቻ በመሆኑ የኮምፒውተሩ ዋጋ ብር 7000.00 በቀጥተኛ የእርጅና አሰላል መሰረት 7000.00/10 = 700.00 ይሆናል፡፡ ይህም በየዓመቱ አስር ዓመት እስኪሞላው ድረስ ብር 700.00 ወጪ ይደረጋል፡፡ እንዲሁም የፅ/መሳርያ ኢንተርፕራይዙ የአንድ ሺ ብር ስለተጠቀመ እና ሀብቱን ከወጪ መለየት ስላለበት ከዚህ እንደሚከተለው ለማየት እንችላለን፡፡

የፅ/መሳርያ ግዥ 1391.30 ሲሆን አገልግሎት ላይ የዋለው የፅ/መሳርያ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡

1391.30 — 1000.00 = 391.30 ቀሪ ይሆናል፡፡ ይህም ማለት ወደ ሀብት የሚሸጋገር ነው፡፡

በዚህ መሰረት ሁለቱንም ማስተካከያ የተሰራላቸው ክስተቶች በጆርናል ስናሳልፋቸው እንደሚከተለው ይሆናሉ፡-

የእርጅና ቅናሽ ወጪን ለመመዝገብ

የእርጅና ቅናሽ ወጪ ------------------ 700.00

የተጠራቀመ የእርጅና ቅናሽ ------------ 700.00

የፅ/መሳርያ ዕላቂ ለመመዝገብ

የፅ/መሳርያ ዕላቂ ወጪ --------------- 1000.00

ፅ/መሳርያ -------------- 1000.00

በመቀጠል ኢንተርፕራይዙ ማስተካከያውን ከሰራ በኋላ የተሰራውን ማስተካከያ ወደተስተካከለ የሂሳብ መሞከሪያ ሚዛን ማስገባት ይኖርበታል፡፡

## የናት የሕ/ሽ/ማህበር

### የተስካከለ የሒሳብ መሞከሪያ ሚዛን

ሰኔ 30/2010 ዓ.ም

ባንክ ገንዘብ -------------------------------------- 149,350.00

የፅ/መሳርያ ------------------------------------------- 391.30

ኮምፒውተር ---------------------------------------- 7000.00

የተ/ዕ/ቅናሽ ------------------------------------------------------------------------ 700.00

ብድር ------------------------------------------------------------------------------------ 1600.00

ቫት ተከፋይ ------------------------------------------------------------------------------- 254.35

ካፒታል ----------------------------------------------------------------------------150,000.00

ሽያጭ ---------------------------------------------------------------------------10,086.95

የማስታወቂያ ወጭ ----------------------------------2500.00

የቤት ኪራይ ወጭ ---------------------------------- 600.00

የኤሌክትሪክ ወጭ ----------------------------------- 200.00

የደሞዝ ወጪ ---------------------------------------- 900.00

የዕ/ቅ/ወጪ ------------------------------------------- 700.00

የፅ/መ/ወጪ --------------------------------------- 1000.00

162,641.30 162,641.30

ወርክሽት የእያንዳንዱን የሂሣብ ርዕስ ከሂሣብ ማስተካከያ በፊት፣ በኋላ እና በማስተካከያ ምዝገባ ወቅት የሚኖረውን ሚዛን እንዲሁም የሂሣብ መግለጫዎችን አካቶ በዝርዝር የሚያሳይ ሠንጠረዥ መልክ ያለው ጊዜያዊ የሥራ መተንተኛ ወረቀት ነው።

| የናት የሕ/ሽ/ማህበር | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ወርክሽት | | | | | | | | |
| | | | | | | | | |
| የሂሳብ አር ዕስት | ያልተስተካከለ የሂሳብ መሞ ከሪያ ሚዛን | | የተስተካከለ የሂሳብ መሞከ ሪያ ሚዛን | | የትርፍና ኪሳራ መግለጫ | | የሀብትና ዕዳ መግለጫ | |
| | ዴቢት | ክሬዲት | ዴቢት | ክሬዲት | ዴቢት | ክሬዲት | ዴቢት | ክሬዲት |
| ባንክ ገንዘብ | 149,350.00 | | 149,350.00 | | | | 149,350.00 | |
| የፅ/መሳርያ | 1,391.30 | | 391.30 | | | | 391.30 | |
| ቫት | | 254.35 | | 254.35 | | | | 254.35 |
| ኮምፒውተር | 7,000.00 | | 7,000.00 | | | | 7,000.00 | |
| የተ/ዕ/ቅናሽ | | | | 700.00 | | | | 700.00 |
| ብድር | | 1,600.00 | | 1,600.00 | | | | 1,600.00 |
| ትርፍ ክፍፍል | | | | | | | | 4,186.95 |
| ካፒታል | | 150,000.00 | | 150,000.00 | | | | 150,000.00 |
| ሽያጭ | | 10,086.95 | | 10,086.95 | | 10,086.95 | | |
| የማስታወ ቂያ ወጭ | 2,500.00 | | 2,500.00 | | 2,500.00 | | | |
| የቤት ኪራይ ወጭ | 600.00 | | 600.00 | | 600.00 | | | |

| | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| የኤሌክትሪክ ወጭ | 200.00 | | 200.00 | | 200.00 | | | |
| የደሞዝ ወጪ | 900.00 | | 900.00 | | 900.00 | | | |
| የዕ/ቅ/ወጪ | | | 700.00 | | 700.00 | | | |
| የፅ/መ/ ወጪ | | | 1,000.00 | | 1,000.00 | | | |
| ድምር | 161,941.30 | 161,941.30 | 162,641.30 | 162,641.30 | 5,900.00 | 10,086.95 | 156,741.30 | 156,741.30 |
| ትርፍ | | | | | 4,186.95 | | | |
| አጠ.ድምር | | | | | | | 156,741.30 | 156,741.30 |

6. የናት የሂሳብ መግለጫ

## የትርፍና ኪሳራ መግለጫ /የገቢና የወጪ/

ገቢና ወጪውን በማመዛዘን ድርጅቱ ማትረፉን /መክሰሩን/ የሚታወቅበት ነው:: በዓመቱ መጨረሻ የተገኘው ውጤት በዓመቱ መጀመሪያ ለማግኘት የታሰበውን ዕቅድ ለመገምገም ያስችላል :: ከላይ በተሰጠው ጥያቄ መሰረት የናት ኢንተርፕራይዝ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ እንደሚከተለው ቀርቧል::

### የናት የሕ/ሽ/ማህበር

የትርፍና ኪሳራ መግለጫ

ከሐምሌ 01 እስከ ሰኔ 30/2010

ሽያጭ ----------------------------------------------------------------10,086.95

የማስታወቂያ ወጭ ------------------------------2500.00

የቤት ኪራይ ወጭ ------------------------------- 600.00

የኤሌክትሪክ ወጭ -------------------------------- 200.00

የደሞዝ ወጪ ------------------------------------- 900.00

የዕ/ቅ/ወጪ ----------------------------------------- 700.00

የፅ/መ/ወጪ -------------------------------------- 1000.00

ጠቅላላ ወጭ ------------------------------------------------------------ 5900.00

ከታክስ በፊት የተገኘ ትርፍ ---------------------------------------------- 4186.95

**ማስታወሻ**

ይህ ኢንተርፕራይዝ ያገኘው ትርፍ በገቢ ግብር ዓዋጁ መሰረት የትርፍ ግብር የተቀመጠበት ስሌት ውስጥ ስላለሆነ ታክስ አይቆረጠበትም ። ነገርግን በሌላ ምሳሌ ከዚሁ ጋር አያይዘን ለማየት ያህል ፤ኢንተርፕራይዙ በዓመት ውስጥ በሽያጭ ያገኘው የብር መጠን 30,000.00 ቢሆንና አጠቃላይ ደግሞ ያወጣው ወጪ ከላይ እንደገለፅነው ሁሉ ብር 5900.00 ቢሆን የሁለቱ ልዩነት ብር 24,100.00 ይመጣል። ስለሆነም በገቢ ግብር ዓዋጁ መሰረት በሰንጠረዥ ሐ ውስጥ የሚገኘው ከብር 19,801- 38,400 በሚለው ላይ ስለሚወድቅ በ15 መቶኛ በማስላት ለገቢዎች የሚሄደውን የብር መጠን ማውጣት ይኖርብናል።

ስሌቱም፡- 24100.00*15/100 — 1710.00 = 1905.00 ይሆናል።

በዚህ መሰረት አጠቃላይ ከታክስ በፊት የተገኘውን ትርፍ ብር 24,100.00 — 1905.00 = 22,195.00 የተጣራ ትርፍ ይሆናል። በተጨማሪም ኢንተርፕራይዙ የዊዝሆልድ ደረሰኞች ቢኖሩት

ወደ ገቢዎች ሊሄድ ከነበረው ብር ላይ ተቀናሽ ተደርጎ የተቀረው ልዩነት ለገቢ ሰብሳቢው መስሪያ ቤት በተዘጋጀው የሂሳብ መግለጫ ቅፅ ላይ በማስፈር ገቢ ይደረጋል።

በመቀጠል ወደ ሀብትና ዕዳ መግለጫ ከመሄዳችን በፊት የኢንተርፕራይዙ አንጡራ ሀብት በተገኘው ትርፍ እንዲሁም ኢንተርፕራይዙ በበጀት ዓመት ውስጥ ከባንክ ያወጡት በአንጡራ ሀብቱ ላይ ለውጥ ስላመጣ ይህንን በአንጡራ ሃብት መግለጫ በማስተካከል ወደ ሀብትና ዕዳ መግለጫ ማካተት ይኖርብናል። በዚህም መሰረት የኢንተርፕራይዙ የአንጡራ ሀብት መግለጫ እንደሚከተለው ተቀምጧል።

## የናት የሕ/ሽ/ማህበር

### የአንጡራ ሀብት መግለጫ

ሰኔ 30/2010

የናት ኢንተርፕራይዝ መነሻ አንጡራ ሀብት --------------------------- 150,000.00

በበጀት ዓመቱ የተገኘ ትርፍ -------------------------------------------------- 4186.95

ሰኔ30/2008 የኢንተርፕራይዙ የመጨረሻ ሚዛን ሲሆን 154,186.95

ማስታወሻ፡- ኢንተርፕራይዙ 4186.95 ትርፍ ያገኘ ሲሆን ይህንን ትርፍ የኢንተርፕራይዙ አባላት ለመከፋፈል በመወሰናቸው ሂሳቡ የትርፍ ክፍፍል ውስጥ ገብቷል፡፤

# የናት የሕ/ሽ/ማህበር

## የሀብትና ዕዳ መግለጫ

## ሰኔ 30/2010 ዓ.ም

## ሀብት

### ተንቀሳቃሽ ሀብት

ባንክ ገንዘብ ------------------------------------------ 149,350.00

የፅ/መሳርያ ------------------------------------------------ 391.30

### ቋሚ ሀብት

ኮምፒውተር ----------------------------------------------- 7000.00

የተ/ዕ/ቅናሽ ----------------------------------------------------------------------------- (700.00)

ጠቅላላ ሀብት ------------------------------------------------------------------------------------------ 156,041.30

## ዕዳ እና እንጡራ ሀብት

ዱቤ የተወሰደ ------------------------------------------------------------------ 1600.00

ቫት ዕዳ --------------------------------------------------------------------------------- 254.35

ትርፍ ክፍፍል --------------------------------------------------------------------- 4186.95

ጠቅላላ ዕዳ ------------------------------------------------------------------------- 6041.30

ዋው ኢን/አንጡራ ሀብት ------------------------------------------------150.000.00

ጠቅላላ አንጡራ ሀብት ------------------------------------------------------------------- 150,000.00

የዕዳና አንጡራ ሀብት ድምር ------------------------------------------------------------ 156,041.30

## የማጠናቀቂያ ምዝገባ

በሂሳብ አያያዝ ስርዓት የሂሳብ መደቦች በአጠቃላይ ጊዜያዊና ቋሚ የሂሳብ መደቦች በመባል በሁለት ዋና ዋና ክፍሎች ይመደባሉ:: ጊዜያዊ የሂሳብ መደቦች የካፒታል መደብ ተቀጥላዎች

ሲሆኑ የድርጅቱ ዓመታዊ ትርፍ ወይም ኪሳራ እስኪታወቅ ድረስ የእያንዳንዱን የገቢና ወጪ ርዕስ ዝርዝር መረጃ ይይዛሉ፡፡

በበጀት ዘመኑ መጨረሻ የትርፍና ኪሳራ መግለጫ ተሰርቶ የትርፍ ወይም የኪሳራው መጠን ሲታወቅ በጊዜያዊ የሂሳብ መደቦች ላይ የሚታየው ሚዛን ወደሚቀጥለው በጀት ዘመን ስለማይተላለፍ በማጠናቀቂያ ምዝገባ ቋሚና ለቀጣይ ዓመት የሚተላለፉት የሂሳብ መደቦች ደግሞ በቀጣይ ዓመት ምዝገባ አማካኝነት ለአዲሱ የበጀት ዘመን እንደመነሻ በሚያገለግለው የእያንዳንዱ ቋሚ የሂሳብ ርዕሶች የገንዘብ መጠን በዝርዝር ይታያል፡፡

ምሳሌው ላይ የተገለፀው ድርጅት በበጀት ዓመቱ የተሰራውን ሥራ በማጠናቀቁ ጊዚያዊ የሆኑ የሂሳብ መደቦች ከዚህ በታች ባለው መልኩ የማጠናቀቂያ መዝገብ ይደረግላቸዋል፡፡

## የሂሳብ መዝገያ

| ቀን | መግለጫ | ማ.ቁ | ዴቢት | ክሬዲት |
|---|---|---|---|---|
| | ሽያጭ(ገቢ) | | 10,086.95 | |
| | የገቢ ማጠቃለያ | | | 10,086.95 |
| | የገቢ ማጠቃለያ | | 5,900.00 | |
| | የማስታወቂያ ወጭ | | | 2,500.00 |
| | የቤት ኪራይ ወጭ | | | 600.00 |
| | የኤሌክትሪክ ወጭ | | | 200.00 |
| | የደሞዝ ወጪ | | | 900.00 |
| | የዕ/ቅ/ወጪ | | | 700.00 |
| | የፅ/መ/ወጪ | | | 1,000.00 |
| | የገቢ ማጠቃለያ | | 150,000.00 | |
| | አንጡራ ሀበት | | | 150,000.00 |

## ምሳሌ 2

### በጥቃቅንና አነስተኛ ኢንዱስትሪ ዘርፍ በማኑፋክቸሪንግ ንዑስ ዘርፍ በልብስ ስፌት ላይ የተሰራ የሂሳብ አያያዝ ማሳያ

ኢቲኦፍ የልብስ ስፌት የህ/ሽርክና ማህበር በሶስት አባላት ሚያዝያ 1/2012 ዓ.ም ብር 10,000.00 እያንዳንዳቸው እኩል በማዋጣት በብር 30,000.00 ካፒታል ስራ ለመጀመር ጀመሩ። በዚህ መሰረት ይህ ኢንተርፕራይዝ የሚከተሉትን የሂሳብ ክስተቶች አከናውኗል። በተጨማሪም የኢንተርፕራይዙ አባላት በመተዳደሪያ ደንባቸው ላይ አባላት በወር ብር 1500.00 ደሞዝ ማግኘት አለባቸው በሚል በተስማሙት መሰረት በወሩ ተከፋይ ይሆናሉ።

1. ሚያዝያ 1 የኢንተርፕራይዙ አባላት በግላቸው ብር ስምንት መቶ በማዋጣት በብር 2400.00 የንግድ ቤት ኪራይ ለ 3 ወራት ተዋዋሉ።

2. ሚያዝያ 2 ለንግድ ፍቃድ ማውጫ፣ለማህተም እና ለደረሰኝ ህትመት በአጠቃላይ ብር 654.00 በደረሰኝ ቁጥር 0121 ክፍያ በግል አዋጥተው በእጅ ከፈሉ።

3. ሚያዝያ 3 የ1 ወር የእፎይታ ግዜ ተሰጥቶት ለ18 ወራት የሚከፈል የወለድ መጠኑ 12% የሆነ ከአነስተኛ ብድር ተቋም ብር 100,000.00 በቼክ ቁጥር 000111 ብድር ወሰዱ።

4. ሚያዝያ 5 የሚከተሉትን ግዥ ፈፀሙ፡-
    1. አንድ ኦቨር ሉክ መምቺያ ማሽን ብር 12,000.00 ከነቫቱ በቼክ ቁጥር 01441 ገዙ።
    2. አንድ የልብስ ሰፌት ማሽን ብር 13,000.00 ቫት ሳይታከልበት ዱቤ ሽያጭ ደረሰኝ 0568 ገዙ።
    3. የተለያዩ ዓይነት የስፌት ክሮች ብዛት 12 የአንዱን ዋጋ ብር 10.00 ከነቫቱ በቼክ ቁጥር 21004 ገዙ።
    4. ለወንበር እና ለጠረጴዛ ግዢ በአንድ ላይ ብር 500.00 ከባንክ ወጪ ተደርጎ ተከፈለ።
    5. አንድ ካውያ በብር 300.00 ከባንክ ወጪ ተደርጎ ተገዛ።

5. ሚያዝያ 5 ብዛቱ 7 የሆነ ለጋዋን፣ለቱታ እና ለዩኒፎርም መስርያ የሚያገለግል ጣቃ ጨርቅ (4ነጭ፣3 ጥቁር) (22.85 ሜትር) የአንዱ ሜትር ዋጋ ብር 90.00 ከነቫቱ በደረሰኝ ቁጥር 0021 በዱቤ ተገዛ።

6. ሚያዝያ 6 አንድ ሰራተኛ ከማህበሩ ጋር ውል በመግባት ወር በገባ በ1ኛው ቀን የሚከፈለው ብር 750.00 በመዋዋል ተቀጠረ።

7. ሚያዝያ 8 ኢንተርፕራይዙ ብር 500.00 በቼክ ቁጥር 00000145 ከባንክ አወጣ።

8. ሚያዝያ 10 ለአድማስ አፀደ ሕፃናት ለ12 ሴት ዕፃናት ቀሚስ እና ለ10 ወንድ ሕፃናት ሱሪ ዩኒፎርም ለማቅረብ ለጨረታ ሰነድ መግዣ አንድ መቶ ብር ከእጅ ከፈለ (የደረሰኝ

ቁጥር 234)፡

9. ሚያዝያ 23 የ20 ሐኪሞች ጋዋን በመስፋት የአንዱን ዋጋ በብር 800.00 በመሸጥ በደረሰኝ ቁጥር 566 በበእጅ ግማሹን ተቀበለ (ቲኦቲ አልተጨመረበትም) ::

10. ሚያዝያ 25 ከተሸጠው ብር ላይ 750.00 በማስቀረት ሌላውን ወደ ባንክ አስገባ (የባንክ በደረሰኝ ቁጥር 8745) ::

11. ሚያዝያ 30 ሞልተው የነበረውን ጨረታ በማሸነፋቸው ለሴቶቹ እና ለወንዶቹ በተመሳሳይ ብር 650.90 ቲኦቲ ሳይጨምር በ15 ቀናት ውስጥ ሰርቶ ለማስረከብ ውል ገባ ::

12. ሚያዝያ 30 የኤሌክትሪክ ክፍያ ብር 175.00 በደረሰኝ ቁጥር 000753455 ከእጅ በገንዘብ ተከፈለ::

13. ግንቦት 2 ለአስተዳደርና ለሽያጭ ክፍል አንድ ሰራተኛ ወር ብር 500.00 ለመክፈል በመወሰን ቀጠሩ በተጨማሪም ከተበደሩት ብድር ውስጥ የመጀመርያ ግዜ ወለድ በቼክ ቁጥር 8888 ከፈሉ::

14. ግንቦት 2 የስልክ ክፍያ ብር 80 በደረሰኝ ቁጥር 00000748 ከእጅ ተከፈለ::

15. ግንቦት 2 ብር 5250.00 ለሰራተኛ እና ለአባላቱ ደሞዝ በቼክ ቁጥር 00512 ተከፈለ::

16. ግንቦት 10 2 ጥቁር ጣቃ ጨርቅ የአንዱን ሜትር ዋጋ ብር 95.00 ከነሻቱ በቼክ ቁጥር 0012356 ገዛ::

17. ግንቦት 17 ያሸነፈውን ጨረታ በሙሉ በማስረከብ ገንዘብ በእጅ ተቀበለ (ት/ቤቱ ዊዝኦልድ ኤጀንት ነው) ::

18. ግንቦት 22 ኢንተርፕራይዙ በዱቤ ወስዷቸው የነበሩትንና ያለበትን ዕዳ በሙሉ ከባንክ በማውጣት በደረሰኝ ቁጥር 7777 ከፈለ::

19. ሰኔ 2 ለሁሉም ሰራተኞች ደሞዝ በቼክ ቁጥር 000012 ተከፈለ እንዲሁም በቼክ ቁጥር 237 ብድሩን ከነወለዱ ከፈሉ::

20. ሰኔ 10 የስልክ ክፍያ ብር 120 በደረሰኝ ቁጥር 00000443 ተከፈለ::

21. ሰኔ 25 የኤሌክትሪክ ክፍያ ብር 300.00 በደረሰኝ ቁጥር 0011024 በቼክ ተከፈለ::

22. ሰኔ 27 9 ኪሎ ብጭቅጫቂ ጨርቅ ጠቅላላ በብር 620.00 ተሸጠ በእጅ ተቀበለ::

**ማስታወሻ**

በቤት ኪራይ ውል ውስጥ ውሃና መብራት ተከራዩ እንደሚከፍል የተዋዋሉ ሲሆን የቤት ኪራይ ሙሉ ለሙሉ ተጠቅመውታል:: በቀጠራ የተገኘ ምንም ዓይነት ኢንቬንቶሪ የለም:: 20 ሱሪ በብር 700.00 ተሸጦ ሳይመዘገብ ቀርቷል::

**ጥያቄ**

1. በትራንሳክሽኑ መሰረት የሂሳብ መደብ እና የሂሳብ መለያ ቁጥር አዘጋጅ
2. ትራንሳክሽኖቹን በጥምር ሂሳብ መዝገብ ላይ አስፍር
3. ወደ ሂሳብ ቋት አሳልፍ
4. የሂሳብ መሞከሪያ ሚዛን አዘጋጅ
5. ማስተካከያ ስራ
6. የሂሳብ መግለጫዎችን አዘጋጅ
7. ከዚህ በታች ያሉትን እንቅስቃሴዎች መነሻ በማድረግ የባንክ ሂሳብ መግለጫ አዘጋጅ
   - ✓ ሰኔ 30/2012 ዓ.ም የባንክ ሂሳብ መግለጫ የመጨረሻ ሚዛን የሚያሳየው ብር 82,766.80 ሲሆን የኢንተርፕራይዙ መዝገብ ላይ የሚታየው ብር 81,816.80 ነው::
   - ✓ ባንክ ሂሳብ መግለጫው ብር 100.00 የአገልግሎት ክፍያ አለው::
   - ✓ የባንክ መግለጫው ከወለድ የተገኘ ገቢ ብር 300.00
   - ✓ ኢንተርፕራይዙ ብር 7,410.00 ባንክ ቢያስገባም በባንክ ሂሳብ መግለጫው ላይ አይታይም
   - ✓ ብር 8160.00 ከደንበኛ የተሰበሰበ ነው::

1. ኢቲኦፍ የልብስ ስፌት የህ/ሽርክና ማህበር የሂሳብ መደቦች እና መለያ ቁጥሮች እንደሚከተለው ቀርቧል።

## ኢቲኦፍ የልብስ ስፌት የህ/ሽርክና ማህበር

### የሂሳብ አርዕስትና መለያ ቁጥር

| የሂሣብ መደቦችና ርዕሶቻቸው | የሂሣብ መለያ ቁጥር | የሂሣብ መደቦችና ርዕሶቻቸው | የሂሣብ መለያ ቁጥር |
|---|---|---|---|
| ሀብት/Assets/ | | 3.አንጡራሀብት /Capital/ | |
| ገንዘብ በእጅ | 101 | ኢቲኦፍ የልብስ ስፌት አን. ሀብት | 301 |
| ገንዘብ በባንክ | 102 | | 302 |
| | | የአባላት አስተዋፅኦ | |
| ዊዝ ሆልዲንግ | 103 | | 303 |
| | | ሪተይንድ ኢህርኒንግ | |
| ቅ/ክ/ የቤት ኪራይ | 104 | | |
| | | 4.ገቢ /Revenue/ | |
| ጥሬ ዕቃ | 105 | | 401 |
| | | ሽያጭ ገቢ | |
| የተመረተ ዕቃ | 106 | | 402 |
| | | ሌሎች ገቢዎች | |
| በምርት ሂደት ላይ ያ | 107 | | |
| | | 5. ግዥ | |
| ቋሚ ዕቃ/ማሽን | 108 | | |
| | | 6. ወጪ /Expenses/ | |
| የተ/ዕርጅ/ቅ/ማሽን/ | 109 | | 601 |
| | | የደመወዝ ወጪ | |
| ካውያ | 110 | | 602 |
| | | የኤሌክትሪክ ወጪ | |
| የተ/ዕርጅ/ቅ/ካውያ/ | 111 | | 603 |
| | | የስልክ ወጪ | |
| ወንበር እና ጠረጴዛ | 112 | | 604 |
| | | የቤት ኪራይ ወጭ | |
| የተ/ዕርጅ/ቅ/ወንበ. ጠረና ጠረ/ | 113 | | 605 |
| | | የዕ/ቅ/ ማሽን ወጪ | |
| | 201 | | 606 |
| ዕዳ /Liability/ | | የዕ/ቅ/ ካውያ ወጪ | |
| | 202 | | 607 |
| ብድር/ከአነስተኛ/ | | የዕ/ቅ/ ወን.እናጠረ. ወጪ | |
| | 203 | | 608 |
| በዱቤ የተወሰደ | | | |
| | 204 | ሌሎች ወጪ | |
| ቲኦት ተከፋይ | | | |
| ተከፋይ የገቢ ግብር | | | |

2. ኢቲኦፍ የልብስ ስፌት ህ/ሽ/ማህበር የሂሳብ እንቅስቃሴውን ተከትሎ የተዘጋጀው የጥምር ሂሳብ መዝገብ እንደሚከተለው ይሆናል።

ሀብት = ዕዳ + አንጡራ ሀብት

30,000.00 = 0 + 30,000.00

የመጀመርያ የሂሳብ መዝገቡ መነሻ ሚዛን ከላይ እንደሚታየው ሲሆን በመቀጠል እያንዳንዱን የሂሳብ እንቅስቃሴ በጥምር መዝገቡ ላይ እንደሚከተለው እናየዋለን፡-

**ኢቲኦፍ የልብስ ስፌት የሀ/ሽርክና ማህበር የህብረት ሽርክና ማህበር ጥምር የሂሳብ መዝገብ**

